ORIGINAL ARTICLE

# Evaluating Ethiopian General Secondary Education Certificate Amharic Examinations Using Bloom`s Cognitive Taxonomy & Their Impact on the teaching-Learning Processes

Agegnehu Tesfa [1]

***Abstract***

*The main purpose of this study is to investigate the compatibility between the Amharic language completion test of the general Secondary Education Certificate education of Ethiopia and the educational objectives of the cognitive domain, the level of relevance and the impact it may have on the teaching-learning process. For these purpose three years 270 questions of the final exams were evaluated according to the matching method used by Weir et al. (1990), Alderson et al.(1995 ).The participating experts are four, two of whom have master's degrees in curriculum and teaching, one in educational assessment and evaluation, and one in teaching Amharic. More information from the officials of the examination agency was also collected by interviewing them. And then, the collected data were analyzed using descriptive statistics. Especially as the analysis of the results of the classification conducted by the experts showed, the relationship between the questions of the tests and the educational objectives of the Bloom`s Cognitive domain was found to be negative. That is, firstly, all the objectives that should be represented in the tests were not represented, and the representation that was represented was questionable. Second, the results of the study showed that the main aspects of the course (application, analysis, synthesis and evaluation) that should be represented by many questions are represented by less than 10% of the questions in the exams. On the other hand, knowledge (recalling, literal Comprehension) that is not (and should not be) given attention in the education policy documents were represented in more than 90% of the questions. This can have a negative impact on the teaching and learning process, which may make students not interested in applying the skills that are presented in their textbooks, which require applying, analyzing, synthesizing and evaluating and higher thinking skills The implication of this is that, firstly, the question writers they choose do not have the ability to come up with questions that consider these objectives; Second, the test preparation capacity building training that is frequently given by the agency to the experts may not bring the desired change in the experts and the questions according to the policy and the attention given to the language education. Based on the findings, the following comments were made; first, the selection criteria of the exam organizers and experts should be revised to enable the selection of appropriate experts, second. If it is possible to facilitate provide lessons and training to the exam organizers and exam preparation experts to ensure that the exams will reflect the objectives the syllabi & textbooks in line with Cognitive domain. Third, for the occurrence of the problems one of the reasons is that the test is offered only by multiple choice method and asking for high level cognitive skills in the multiple choice test may require different experience and skills, if a system should be developed where the tests prepared are not only multiple choice method as is being done in many other countries.*

**Keywords**: *cognitive category, completion tests, test Correlation, test impact.*

*1. Assistant Professor of Amharic, University of Gondar. Email:agetesfa@gmail.com*

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና ከአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ/ ተዛምዶ፣ የተዛምዶ ደረጃና በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ ሊያሳድረው የሚችለውን ተጽዕኖ መፈተሽ ነው። ይህን መሰረታዊ ዓላማ ለማሳካትም የሦስት ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች 270 ጥያቄዎች በዌር እና ሌሎች (1990)፣ ኦልደርሰንና ሌሎች(1995)፣ ችዱ (2010) እና ታንግስኩል (2017)ዓ.ም ስራ በተመለከተው የማዛመጃ ዘዴ መሰረት ከአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች ጋር በማዛመድ ተገምግመዋል። የፈተናዎቹን ጥያቄዎች ከአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች ጋር በማዛመድ የተሳተፉት ባለሙያዎችም አራት ሲሆኑ ሁለቱ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በሥርዓተ ትምህርትና ማስተማር፣ አንዱ በትምህርታዊ ሥነ-ልቦናና በምዘናና ግምገማ አንዱ አማርኛን በማስተማር የሰሩ የኮሌጅ መምህራን ናቸው። ተጨማሪ መረጃዎች ከፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች በቃለ መጠይቅ ተሰብስበው ተተንትነዋል። በተለይ በባለሙያዎቹ የተካሄደው ምደባ ውጤት ትንተና እንዳሳየውም፣ የፈተናዎቹ ጥያቄዎች ከአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች ጋ ያላቸው ዝምድና አሉታዊ ሆኖ ተገኝቷል። ይኸውም አንደኛ በፈተናዎቹ መወከል ያላባቸው ዓላማዎች ሁሉ አልተወከሉም፣ የተወከሉት ውክልናም ተጠየቃዊ/ሎጅካል ሆኖ አልተገኘም። ሁለተኛ በብዙ ጥያቄ ሊወከሉ የሚገባቸው ዋነኛዎቹ የትምህርቱ ጉዳዮች (ትግበራ፣ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ) በፈተናዎቹ እየተወከሉ ያሉት ከ10% በሚያንሱ ጥያቄዎች ብቻ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። በአንጻሩም በትምህርት ፖሊሲ ሰነዶች ትኩረት ያልተሰጣቸው (ሊሰጣቸውም የማይገባቸው) እውቀት/ ማስታወስና ግንዛቤ/መረዳት ከ90% በላይ በሚሆኑ ጥያቄዎች የመወከል እድል እንዳገኙ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። ይህም ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፎቻቸው የቀረቡ መተግበርን፣ መተንተንን፣ ማቀናበርንና መገምገምን የሚጠይቁ የክሂል ትምህርቶችን ተግባራዊ የማድረግ ፍላጎት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ በመማርማስተማር ሂደቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ነው። በተለይ ከክሂሎች ጋር የተያያዙ ከፍተኛ የማሰብ ችሎታዎችን የሚፈልጉ በተግባር እንዲጽፉ፣ እንዲወያዩ፣ እንዲከራከሩ፣ ንግግር እንዲያደርጉ ወዘተ. የሚያዙትን መልመጃዎች ፈቃደኛ ሆነው እንዳይሰሩ የሚያበረታታ ነው። የዚህም አንድምታ የፈተናዎች ኤጀንሲ አንደኛ፣ የሚመርጣቸው ጥያቄ አውጭዎች/ ጸሐፊዎች እነዚህን ዓላማዎች ያገናዘቡ ጥያቄዎች የማውጣት/ የመጻፍ አቅም/ ክሂል የላቸውም፤ ሁለተኛ፣ በኤጀንሲው ለየትምህርት ዓይነቶቹ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች በተደጋጋሚ እየተሰጠ ያለው የፈተና አዘገጃጀት አቅም ማጎልበቻ ስልጠና በባለሙያዎቹ ላይ የሚፈለገውን ለውጥ አስገኝቶ ፈተና አዘጋጆቹ (ጥያቄ ጸሐፊዎች) የሚያወጧቸው ጥያቄዎች፣ እነዚህን ዓላማዎች በፖሊሲውና በቋንቋው ትምህርት በተሰጣቸው ትኩረት መሰረት የሚወከሉበትን አቅጣጫ ማሳየት አላስቻላቸውም የሚል ነው። ከጥናቱ ግኝቶች በመነሳትም የሚከተሉት አስተያየቶች ተሰጥተዋል፤ አንደኛ. የፈተና አዘጋጆችና ባለሙዎች መምረጫ መስፈርቶች ተገቢ ባለሙያዎችን መምረጥ የሚያስችሉ ተደርገው ቢዘጋጁ/ ቢከለሱ፣ ሁለተኛ. የሚዘጋጁት ፈተናዎች ከትምህርቱ ጋር የሚጣጣሙ እንዲሆኑ ማድረግ የሚያስችሉ ትምህርቶችና ስልጠናዎች ለፈተና አዘጋጆችና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች የሚሰጥበትን መንገድ ማመቻቸት ቢቻል። ሦስተኛ፣ ለችግሮቹ መከሰት አንዱ መንስኤ ፈተናው በምርጫ ብቻ የሚቀርብ በመሆኑና በምርጫ ፈተና ከፍተኛ ደረጃ የአዕምሯዊ ችሎታዎችን መጠየቅ የተለየ ልምድንና ችሎታን ሊጠይቅ ስለሚችል በብዙ ሀገሮች እየተደረገ እንዳለው የሚዘጋጁት ፈተናዎች ምርጫ ብቻ የማይሆኑበት ሥርኣት ቢዘረጋ።

**ቁልፍ ቃላት፡- አዕምሯዊ ምድብ፣ ማጠናቀቂያ ፈተናዎች፣ ተጣጥሞሽ፣ የፈተና ተጽዕኖ**

## መግቢያ

የአጠቃላይ ትምህርት መስክም ሆኑ የቋንቋ ፈተና ተመራማሪዎች (ለምሳሌ ግሮላንድ 1976፣ ኢቤል 1979፣ ተሾመ 1995፣ ሁዝ 2003) እንደሚያስረዱት በትምህርት ሥርዓት ፈተናና ትምህርት የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ “ተማሪዎች የተማሩትን ምን ያህል መሥራት ችለዋል ? ብሎ የማይገመግም ማስተማር አለ ብሎ ማሰብ አይቻልም” የሚለው የኦልደርሰን (1999) አገላለጽም ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፈተና ዕውቀትን ማሻሻያና የአንድን የትምህርት ተቋም ሀላፊነቱን የመተግበር ደረጃ ማሳደጊያ ነው ተብሎም ይታመናል (ሾሃሚ 2000)፡፡ በብዙ ሀገሮች የትምህርት ሥርዓት በአግባቡ እየተከናወነ እንደሆነ መቆጣጠሪያ ተደርጎም ይታያል፡፡ የዚህ መሰረታዊ መነሻም በዳግላስ (2010) እና ሄኒንግ (1987) እንዲሁም በኢቤል (1979) ስራዎች እንደተመለከተው ልብስ በሜትር፣ እንቁላል በቁጥር፣ ወተት በሊትር እንደሚለካ ሁሉ የማስተማር- መማር ሂደት የመጡ ለውጦች/ የታዩ ዕደገቶች ዋነኛ ሳይንሳዊ መለኪያ/ መመዘኛ ፈተና ስለሆነ ነው፡፡

በእርግጥ አያሌ በፈተና ላይ ምርምር የሚያካሂዱ ምሁራን (ለምሳሌ ግሩላንድ 1976፣ ኢቤል 1979፣ ዳግላስ 2010‹ ተሾመ 1995፣ ሄኒንግ 1987) እንደሚያስረዱት በትምህርት ሥርዓት የተለያዩ ፈተናዎች ለተለያየ ዓላማ ይዘጋጃሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በማስተማር-መማር ሂደት ላይ የሚከሰቱ /የተከሰቱ ችግሮችን ለመለየት የሚዘጋጁ ፈተናዎች አሉ፡፡ ይህ የፈተና ዓይነት በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት የትኛዎቹ ተማሪዎች የተሻለ ችሎታ እንዳላቸው፣ የትኛዎቹ ደግሞ ድክመት እንዳለባቸው መለየትን ዓላማ አድርጎ የሚዘጋጅ ነው (ሄኒንግ 1987፣1)፡፡ ሁለተኛው የፈተና አይነት የተማሪዎችን ችሎታ ለመለየትና ለመምረጥ (Screening & Selection) የሚዘጋጀው የብቃት መለኪያ (Proficency) ፈተና የሚባለው ነው:: ለምሳሌ

ለቀጣዩ የትምህርት ፕሮግራም /ደረጃ ብቁ የሆኑ ተማሪዎች/ ግለሰቦች የትኞቹ ናቸው? የሚለውን ለመወሰን የሚያስችል መረጃ ለማግኘት የሚዘጋጁ ፈተናዎች በዚህ የፈተና ዓይነት ስር ይመደባሉ፡፡ ምክንያቱም በማንኛውም ሁኔታ የመምህራን ቁጥርና የፋሲሊቲ ውስንነት ስለሚኖር ሁሉንም ተማሪ ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ ለማዛወር/ ለማሸጋገር ስለማይቻልና የተሻሉ ተማሪዎችን መለየትና መምረጥ ግድ ስለሚሆን ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የፈተና ዓይነት የተሻሉ ተማሪዎችን የመለያና የመምረጫ መንገድ ተደርጎ ይወሰዳል (ሂኒንግ 1987)፡፡

ሦስተኛው የፈተና አይነት/ዓላማ የተማሪዎችን ችሎታ(Achivement) ለመመዘን ወይም አንድን የትምህርት ፕሮግራም ለመገምገም የሚዘጋጅ የፈተና ዓይነት ነው፡፡ የተማሪዎችን ችሎታ ወይም የአንድን ትምህርት ፕሮግራም ውጤታማነት ለመገምገም የሚያስችል መረጃ ለማግኘት የሚዘጋጅ የፈተና ዓይነት ነው (ሄኒንግ 1987፣ ተሾመ 1995፣ ዳግላስ 2010)፡፡ ወደኋላ ሰፋ ብሎ እንደተገለጸው በዚህ ጥናት ችሎታ ከነብሉም አዕምሯዊ የትምህርት ዓላማዎች አንጻር የተማሪዎችን የማወቅ፣ የመረዳት፣ የመተግበር፣ የመተንተን፣ የማቀናበርና የመገምገም ብቃት ደረጃን የሚመለከት ነው፡፡

ከፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና ከአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ጋር ከተካሄዱት ቃለ መጠይቆች መረዳት እንደተቻለው የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተናዎች የሚዘጋጁት ከላይ ከተጠቀሱት ዓላማዎች መካከል ሁለተኛውና ሦስተኛው ላይ ተመስርተው ነው፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያ ሁኔታ የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ/ ብሔራዊ ፈተናዎች ሁለት ዓላማዎችን መሰረት አድርገው የሚዘጋጁ ናቸው ማለት ነው፡፡ ከሁለቱ ቀዳሚውና ዋነኛው ዓላማ ተማሪዎች የ፪ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ማጠናቀቃቸውን መመስከር ነው፡፡ ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ / መሰናዶ ትምህርት ማለፍ/ መዛወር ያለባቸውን ተማሪዎች ለመለየትና ለመምረጥ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ፈተናዎች እንደገና የክፍል(Class room)ና ውጫዊ(Public) ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡ ፡ የክፍል የሚባሉት ብዙውን ጊዜ በትምህርት ቤት ደረጃ በየትምህርት ዓይነቶቹ መምህራን በየሲሚስተሩ የሚዘጋጁ ፈተናዎች ናቸው፡፡ ውጫዊ የሚባሉት ደግሞ ከትምህርት ቤት ውጭ በሆነ ተቋም/ድርጅት የሚዘጋጁ ፈተናዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያ ሁኔታ በፈተናዎች ኤጀንሲ የሚዘጋጁት የማጠናቀቂያ/ ብሔራዊ ፈተናዎች ውጫዊ ፈተናዎች ናቸው፡፡ ውጫዊ ፈተናዎች (High Stake Tests) ከፍተኛ ውሳኔ የሚወሰንባቸው ፈተናዎች በመባልም ይታወቃሉ፡፡ በተለያዩ ተመራማሪዎች (ለምሳሌ በሾሃሚንና ሌሎች 1996፣ ዎል 2005) ስራዎች እንደተገለጸው የውጫዊ ፈተናዎች አንዱ ሚና አንድ የትምህርት ሥርዓት በታለመው መንገድ በሁሉም ትምህርት ቤቶች እየተከናወነ እንደሆነ ለመቆጣጠር ወይም በየትምህርት ቤቶቹ ወጥ/ ተመሳሳይነት ያለው ትምህርት እንዲሰጥ ለማበረታታት ነው፡፡ ፖሊሲ ነዳፊዎች የትምህርት ሥርዓቱ በታሰበው መንገድ እየተካሄደ መሆኑን የሚቆጣጠሩትም በውጫዊ ፈተናዎች አማካኝነት ነው፡፡

ውጫዊ ፈተናዎች መምህራን ምንና እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው የማመላከት፣ ተማሪዎችም ለመማር እንዲነሳሱ የማድረግ ሀይል እንዳላቸው ለምሳሌ የችንግ (1997)፣ ሾሃሚና ሌሎች (1996) ጥናቶች ውጤት አመላክተዋል፡፡ ማድሰን (1988) "መምህራን ምን ማስተማርና እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው፤ እንዲሁም ተማሪዎች ምን መማርና እንዴት መማር እንዳለባቸው የመወሰን አቅሙ እየጎለበተ እየመጣ ያለው መደበኛ ሥርዓተ ትምህርቱ ሳይሆን ፈተና ነው፤" ይላሉ፡፡ ታይለር (2005) እና አበበ (1990) ይህንኑ ሐሳብ ይጋራሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ውጫዊ ፈተናዎች የማስተማር መማር ሂደቶችን አቅጣጫ በማስያዝ ወይም በማስቀየር ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በእርግጥ በማስተማር መማር ሂደቶች ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል (ችንግ 1997፣ ሾሃሚንና ሌሎች 1996፣ ተሾመ 1995)፡፡ ብዙ ጊዜ ፈተናዎች አዎንታዊ ሚና የሚኖራቸው አዘገጃጀታቸው ጥሩ መማርን የሚያበረታታ ሲሆን ነው፡፡ ተጽዕኗቸው አሉታዊ የሚሆነው ደግሞ የፈተናዎቹ ዝግጅት የትምህርት ፖሊሲና የሥርዓተ ትምህርቶቹ

ዓላማዎች ነጸብራቅ ሳይሆን ሲቀር ነው (አበበ 1990፣ ማዳስ 1988 ኦልደርሰን 1999፣ ሳዲክ 2010)፡፡

የፈተናዎች ተጽዕኖ እየታወቀ በመምጣቱም ብዙ ሀገሮች (ለምሳሌ ሆንግኮንግ፣ ታይዋን፣ ጃፓን፣ ቻይና) ውጫዊ ፈተናዎቻቸው ጥሩ መማርን የሚያበረታቱ እየሆኑ እንዲዘጋጁ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ዐውድም ፈተናዎች የሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ ሰነዶችና ሰነዶቹ መሰረት ያደረጓቸው የነብሉም አዕምሯዊ ምድብ ዓላማዎች በተለይም ከፍተኛ ትኩረት ለተሰጣቸው ከፍተኛ ደረጃ የማሰብ ክሂሎች (higher Order Thinking Skills) ነጸብራቅ/ ወካይ ሊባሉ የሚችሉ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡ ፡ ወካይ የሚሆኑ ከሆኑ ደግሞ ፈተናዎቹ እነዚህ ክሂሎች በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ትኩረት እንዲሰጣቸውና በትምህርቱ አሰጣጥ ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ አዎንታዊ እንዲሆን የሚያደርጉት ተጽዕኖ ከፍተኛ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡ በተቃራኒው በነብሉም ስራ እንደተገለጸው በኑሩ (1992) ጥናትም እንደተንጸባረቀው የፈተናዎቹ ጥያቄዎች በዝቅተኛ ችሎታነት በሚታወቁት በማስታወስና በመረዳት ላይ የሚያተኩሩ ከሆነ ፈተናዎቹ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ሊያንጸባርቁት የሚችሉት ተጽዕኖ አሉታዊ ሊሆን ይችላል፡፡

ይህ ጥናት የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ የነብሉም የአዕምሯዊ ምድብ ዓላማዎች አንደኛ ምን ያህል እንደሚንጸባርቁ ፣ ሁለተኛ ከፍተኛ የሚባሉ የዚሁ ምድብዓላማዎች ውክልና ምን እንደሚመስል እና ሦስተኛ ጥያቄቹ ከእነዚህ ዓላማዎች ውክልና አንጻር ሲፈተሹ አዎንታዊ መማር- ማስተማርን የሚያበረታቱ መሆን አለመሆናቸውን የሚመረምር በመሆኑ የአምሯዊ ምድቡን የተወሰኑ ገጽታዎችና ስድስቱን ዓላማዎች በጥልቀት ባይሆንም በቅኝት መልክ ከዚህ ቀጥሎ ለማንሳት ተሞክሯል፡፡

## በፈተናና በትምህርት ዓላማዎች መካከል ያለ ተጣጥሞሽ *(Overlapping)*

ቀደም ብሎ በተወሰነ ደረጃ ለመጠቆም እንደተሞከረው በአንድ የትምህርት ሥርዓት አንዱ የፈተና አዎንታዊ ተጽዕኖ ማበረታቻ ስልት ፈተናዎች ከአጠቃላይ የትምህርት ዓላማ ምድቦችም ሆነ ከትምህርቱ ዓይነት ሥርዓተ ትምህርት ጋር ተገቢ ዝምድና እንዲኖራቸው ማድረግ መቻል ነው፡፡ ስለዚህ ውጫዊ/ ብሄራዊ ወይም የክፍል ፈተናዎችን ከአጠቃላይ የትምህርት ዓላማዎች ጋም ሆነ ከትምህርቱ ዓይነት ሥርዓተ ትምህርት ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ እንዲኖራቸው ማድረግ ይጠበቃል፡፡ ከዚህም ፈተናዎች እንዲኖራቸው የሚጠበቀው ተዛምዶ ሁለት አቅጣጫ ያለው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ አንደኛው ከአጠቃላይ የትምህርት ዓላማዎች ጋር ሲሆን ሁለተኛው ከራሱ ከትምህርት ዓይነቱ ዓላማዎች/ ይዘቶች ጋር ነው፡፡ በተለይ የምርጫ ፈተና ከሆነ በአጠቃላይ ትምህርት ዓላማነት ከሚታወቁት ሦስት ምድቦች (Domains) መካከል ከአዕምሯዊ ምድብ (Cognitive Domain) ስድስት የትምህርት ዓላማ ክፍሎች/ ችሎታዎች ጋር ፈተናዎች ተገቢ የሚባል ዝምድና እንዲኖራቸው ይጠበቃል፡፡ በዚህ ጥናት የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹን ተጣጥሞሽ/ ዝምድና ለመመርመር የተሞከረውም ከእነዚህ አጠቃላይ ትምህርት አዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች ዓላማዎች ጋር ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ቀጥሎ ስለአጠቃላይ አዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎችና ፈተና ግንኙነት መሰረታዊ የሚባሉ ጉዳዮችን ከአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች መዳበር ታሪካዊ ዳራ በመነሳት ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች/ችሎታዎችና የፈተና ጥያቄዎች ተጣጥሞሽ ቀደም ብሎ እንደተወሳው በመደበኛ ትምህርት የክፍልም ሆነ የማጠናቀቂያ (public) ፈተናዎች የሚዘጋጁት በአብዛኛው የትምህርት ዓላማዎች ምን ያህል እንደተሳኩ /ለስኬት እንደበቁ ለማረጋገጥ ነው፡፡ በአጠቃላይ ትምህርት መስክ ምሁራን በተለይም በምዘናና ግምገማ (measurement and evaluation)፣ በሥርዓተ ትምህርትና መሰል መስኮች ባለሙያዎች ተደጋግሞ እንደሚገለፀው መደበኛ ትምህርትን መሰረት የሚያደርግ ምዘና

በተለይም የችሎታ መለኪያ ፈተና ሲዘጋጅ የትምህርትን ባሕርያዊ ዓላማዎች (Taxonomy of behavioral objectives) (ከትምህርት ዓይነቱ ዓላማ ምድቦች በተጨማሪ ማለት ነው) ማንፀባረቅ ይኖርበታል (ደሳለኝ 2005፣ አንደርሰንና ሌሎች 2001)። በዚህ ረገድ በተለያዩ ምሁራን (ለምሳሌ አበበ 1990፣ ራኒ እና ሌሎች ፣ 2004፤ ሳክስ፣ 1974፤ ግሩላንድ 1976፣ ሙንዝኔር እና ሩቢን፣ 2013) እንደተገለፀው ዋነኛው የመማር ተጠባቂ ውጤቶችን (Learning outcomes) ለመለካት የሚያገለግለውና ለብዙ ዓመታት በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ሰፊ ተቀባይነት እንዳገኘ የቀጠለው ብሉም እና ባልደረቦቻቸው ያዳበሩት አዕምሯዊ የትምህርት ዓላማዎች ምድብ (cognitive domain) የሚባለው ማዕቀፍ (framework) ነው። ይህ ማዕቀፍ ከዳበረ ብዙ ዓመታት የተቆጠሩ ቢሆንም በዓለም ላይ ተቀባይነቱ ከፍ እያለ ነው የመጣው። በእርግጥ የብሉም ተማሪ የነበሩት አንደርሰን በ(2001) ላይ የብሉምን አዕምሯዊ ምድቦች አንደኛ ቅንበራ የሚለውን መፍጠር በሚለው ለመተካት፤ ደረጃውንም ከግምገማ በኋላ ለማምጣት፣ ሁለተኛ ስያሜዎችን ከስምነት ወደግስነት በመቀየር ዕውቀትን ማስታወስ፣ ግንዛቤን መረዳት፣ ትግበራን፣ መተግበር፣ ትንተናን፣መተንተን፣ ግምገማን መገምገም በማለት ለመከለስ (revised) ጥረት ያደረጉ ቢሆንም (ችዱክ 2008፣ ሽሬቪጉና ሌሎች 2010 ፣ ታንግሰኩልና ሌሎች 2017) አከፋፈሉ ሰፊ ተቀባይነት አላገኘም (ሙንዝኔር እና ሩቢን፣ 2013)። በመሆኑም ይህ ጥናት ዋነኛ ማዕቀፍ ያደረገው ቀዳሚውን የዶክተር ብሉም አከፋፈል ሲሆን አዲሱ በማጠናከሪያነት እንዲያገለግል ተደርጓል።

በብሉምና ሌሎች የዳበረውም ሆነ በተማሪያቸው የተከለሰው አዕምሯዊ ምድብ የዕውቀት፣ የማስታወስና የማሰብ ችሎታን በማዳበር ላይ የሚያተኩር ነው። አዕምሯዊ ምድብ ከተራ ማስታወስ እስከ ውስብስብ ግምገማ የሚደርሱ በመማር የሚመጡ የማሰብ ችሎታ ክሂሎች (intellectual skills) ተዋረዳዊ (hierarchical) እድገቶች የተካተቱበት ነው (ሳክስ፣ 1974፣ ሽሬቪጉና ሌሎች 2010፣ ታንግሰኩልና ሌሎች 2017)። በሌላ አገላለፅ አዕምሯዊ ምድብ አዕምሯዊ ክሂሎችን

(mental skills) በማዳበር ላይ የተመሰረተ የትምህርት ዓላማ ምድብ ነው ማለት ይቻላል። ይህ አዕምሯዊ የትምህርት ዓላማ ምድብ ለማስተማር፣ ለመማርና ለግምገማ መሰረት ሆኖ የሚያገለግል ነው (ሙንዝኔርእና ሩቢን፣ 2013፣ ችዱክ 2008፣ ሽሬቪጉና ሌሎች 2010 ፣ ታንግሰኩልና ሌሎች 2017)። ምድቡ በውስጡ ዕውቀት፣ ግንዛቤ፣ ትግበራ፣ ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ የሚባሉ ስድስት መሰረታዊ ክፍሎች (categories) የተካተቱበት ሲሆን ክፍፍሉም ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከተራ ወደ ውስብስብነት እያደገ የሚሄድ ነው። በውስብስብነት ደረጃ ተከታዩ ከቀዳሚው ላቅ ያለ ብቻ ሳይሆን በቀዳሚው ላይ የሚመሰረትም ነው። በራኒ እና ሌሎች (2004) አገላለጽ ፩ኛው ለሁለተኛው፣ አንደኛውና ሁለተኛው ደግሞ ለሦስተኛው እንዲሁም ከ1-5 ያሉት ለስድስተኛው ቅድመ ተከዋኞች (prerequisites) ናቸው።

በሳክስ (1974፡ 57) ጥናት እንደተገለጸው ብሉም እና የስራ ባልደረቦቻቸው (1956) እነዚህን የአዕምሯዊ ምድብ ስድስት ክፍሎች ዓላማዎች በዚህ መንገድ ከፋፍለው ለማቅረብ ከተገፋፉባቸው ምክንያቶች አንዱ ተማሪዎች በአንድ የትምህርት ሥርዓት በማለፍ በግል ማከናወን ወይም ማሰብ የሚኖርባቸውን የታለሙ ባህርያት በግልፅ ለማሳየት ነው። የክፍፍሉ ሂደትም የክፍሎችን (የሚገለፁትን ጉዳዮች) ውጫዊና ውስጣዊ (ግልጽና ስውር) ባህርያት (Implicit and overt behaviors)፣ እንዲሁም የውስብስብነት (complexity) ደረጃ መሰረት ያደረገ ነው። ሳክስ (1974) አክለው እንደገለፁት ተማሪዎች ምን እንደሚማሩ ሳይታወቅ የፈተና ጥያቄንና ምድብን (domain) ለመመርመር መምከር አስቸጋሪ ነው። በብሉም (1956) የተካሄደው የአዕምሯዊ ምድብ ክፍፍል ይህን ችግር ለመፍታት ጠቃሚ ዘዴ ሆኖ ተገኝቷል። ለመምህራንም ከፈተና በፊት ሲያስተምሩ ሊያተኩሩባቸው የሚገቧቸውን ዓላማዎች እንዲያውቁ የሚያስችላቸው ስራ ሆኖ አግኝተውታል። ይህም ሌላው የአዕምሯዊ ትምህርት ዓላማዎችን በተለያዩ ክፍሎችና ደረጃዎች የመመደባቸው ተግባር ውጤት ነው (ሳክስ፣ 1974፣ 57፣ አንደርሰን 2001)።

በተለያዩ የመስኩ ምሁራን፣ በተለይም በሙንዘኒየር እና ሩቢን (2013) ስራ በዝርዝር እንደቀረበው ብሉም የትምህርት ዓላማዎችን ድልድል (Taxonomy of educational objectives) ለማዳበርና በደረጃ ለመከፋፈል ሲጀምሩ ዋነኛ ዓላማቸው የነበረው የትምህርት ምዘና ባለሙያዎች (experts) ግኝቶቻቸውን እንዲጋሩና የፈተና ጥያቄዎቻቸውን እንዲቀያየሩ (ሐሳብ እንዲለዋወጡ) የሚያስችል የጋራ መግባቢያ እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው፡፡ በዚህ ሐሳብ መነሻነት የዳበረው አዕምሯዊ የትምህርት ዓላማዎች ክፍፍልም ተቀባይነት አግኝቶ ከ22 በማያንሱ ቋንቋዎች ተተርጉሞ እስከዛሬ ድረስ በዓለም የትምህርት ሥርዓት ሰፊ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ የመማር ክፍሎች ገለፃም ሆነ የውስብስብነት ደረጃቸውን የሚያሳየው ተዋረድ (levels of intricacy) እስካሁን ሰፊ ተቀባይነት እንዳገኘ ነው (ሙንዘኒየርr እና ሩቢን፣ 2013)፡፡ አንድ ፈተና አዎንታዊ የመማር ማስተማር ሂደትን ሊያበረታታ የሚችለውም እነዚህን በአዕምሯዊ ምድብ ስር የተካተቱ የመማር ደረጃዎችን በአገናዘበ መልኩ መዘጋጀት ሲችል ነው፡፡

አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ለማስተማር፣ ለመማርና ለምዘና (ግምገማ) መሰረት ሆኖ እያገለገለ ያለው ይህ የብሉም አዕምሯዊ ምድብ) ከመዳበሩ በፊት ብሉም ካከናወኗቸው ተግባራት አንዱ የፈተና ጥያቄዎች ትኩረት በምን ላይ እንደሆነ መመርመር ነበር፡፡ በምርምራቸውም ከ95% በላይ በፈተናዎች የሚካተቱ ጥያቄዎች ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ ማስታወስ መቻላቸውን የሚለኩ ሆነው አግኝተዋቸዋል፡፡ ይህ አዕምሯዊ የትምህርት ዓላማዎች ድልድል በትምህርት ሥርዓት ትኩረት እያገኘና የማስተማር፣ የመማርና የምዘና ማዕቀፍ እየሆነ ከመጣ ከ40 ዓመት በኋላ ደግሞ ዝቅተኛ የአዕምሯዊ ችሎታ ደረጃን የሚመዝኑ ጥያቄዎች (lower-order assessment questions) መጠን ወደ 70% ዝቅ እንዳሉ ብሉም ማመልከታቸውን በሙንዘንሚየር እና ሩቢን (2013) ሥራ ተገልጧል፡፡ ይህም ፈተና አዘጋጆች የሚያወጧቸው ጥያቄዎች የተማሪዎችን የማስታወስ ችሎታና ጥልቅ አስተሳሰብ የሚያካትቱና መካተታቸውን የሚያበረታቱ እየሆኑ መምጣታቸውን የሚያሳይ ነው (ሙንዘንሚየር እና ሩቢን 2013)፡፡

እነዚህ የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓትም በፖሊሲ ደረጃ ሳይቀር ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ስለዚህ በተለይ በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውና በሥርዓተ ትምህርት ማስፈጸሚያ ማዕቀፉ የተሰጣቸውን ትኩረት በተመለከተ የተወሰኑ ሀሳቦችን ማንሳት ያስፈልጋል፡፡ ከዚያ በፊት ግን በጥናቱ ውክልናቸው የሚፈተሸውን ስድስቱን የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች በተናጠል እያነሱ ምንነታቸውን፣ መለያ ባሕርያቸውን/ ገፅታዎቻቸውንና የሚጠቀሙባቸውን መሰረታዊ ወይም ቁልፍ ቃላት ቢያንስ በአጭር በአጭሩ መመልከት ያስፈልጋል፡፡

### ሀ. ዕውቀት/ማስታወስ (Knoweledge/ Remembering)

"ዕውቀት"(ማስታወስ) የሚባለው ችሎታ ከስድስቱ አዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች የመጀመሪያውና ዝቅተኛ የመማር ደረጃን (የመማር ውጤትን) የሚወክል ክፍል (category) ነው፡፡ በዚህ በእውቀት ደረጃ ዓላማዎች፣ ከተማሪዎች የሚጠበቀው ችሎታ ቀደም ብለው የተማሩትን ማስታወስ መቻል ነው፡፡ እንዲያስታውሱ የሚጠበቀውም የተማሯቸውን እውነታዎች (facts)፣ መረጃዎች፣ መርሆዎች፣ ቲዎሪዎችና መሰል ጉዳዮች ነው፡፡ በዚህ ዝቅተኛ በሚባለው አዕምሯዊ ክፍል ደረጃ ተማሪዎች መልስ መስጠት እንዲችሉ የሚጠበቅባቸውም ማን፣ ምን፣ መቼ፣ የት፣ ወዴት… ለሚሉት ጥያቄዎች ሲሆን የጥያቄዎቹ አቀራረብም፣ መልሱ፣ ዘርዝሩ፣ አስታውሱ፣ ደግማችሁ ተናገሩ የሚሉ ዓይነት ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ደረጃ ከተማሪዎች የሚጠበቀው ችሎታ የተለመዱ ቃላትን፣ የተወሰኑ እውነታዎችን፣ አንዳንድ ዘዴዎችንና ቅደም ተከተሎችን (procedures)፣ መሰረታዊ ፅንሰ ሐሳቦችንና መርሆዎችን ማወቅ መቻል ነው (አበበ 1991፣ ግሩላንድ 1976፤ ሳክስ፣ 1974፣ችዱክ 2008፣ ቨሬቪጉና ሌሎች 2010፣ ታንግሰኩልና ሌሎች 2017 እንዲሁም ሙንዘንሜየር እና ሮቢን

2013):: የዚህ ምድብ ቅድመ ተከውኖ (prerequisite) እስካሁን አይታወቅም (ራኒ እና ሌሎች፣

2004፣ 151)፡፡

## ለ.ግንዛቤ/ መረዳት (Comprehension/ Understanding)

ግንዛቤ/መረዳት ከዕውቀት ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃነት የሚመጣ ችሎታ ነው፡፡ በአብዛኛው ተማሪው ያዳመጠውን ወይም ያነበበውን (የተላለፈውን መልዕክት) ምን ያህል ተረድቶታል? የሚለውን የሚመለከት ክፍል ነው፡፡ ስለዚህ ከማስታወስ (ከመሸምደድ) አንድ ደረጃ ከፍ ቢልም በዝቅተኛ ችሎታነት የሚመደብ ነው፡፡ እውነታዎችንና መርሆዎችን፣ ሠንጠረዦችንና ግራፎችን፣ እንዲሁም የቃላትን ፍቺ መረዳት፣ በቋንቋ (በቃላት) የተገለፁ ሐሳቦችን ወደ ቁጥር መቀየር፣ ከቀረበው መረጃ ተነስቶ ቀጥሎ ሊከሰት የሚችልን ጉዳይ መተንበይ፣ የዘዴዎችንና አሰራሮችን ተገቢነት ወዘተ ማስረዳት መቻል በዚህ በሁለተኛው አዕምሯዊ ምድብ ክፍል እንዲዳብሩ የሚጠበቁ የትምህርት ዓላማዎች ናቸው (አበበ 1990፤ ግሩላንድ 1976፤ ሳክስ 1974፤ ሙንዘንሜየር እና ሩቢን 2013፤ ራኒ እና ሌሎች 2004)፡፡

በዚህ በሁለተኛው አዕምሯዊ ደረጃ በተማሪዎች እንዲመለሱ የሚጠየቁ ጥያቄዎችም የተረዱትን በራሳቸው አባባል መግለፅን፣ እንደገና መጻፍን፣ ምሳሌ መስጠትን፣ መበየንን፣ ጨምቆ ማቅረብን (summarizing)_ ለምሳሌ በቋንቋ ትምህርት ዋና ዋና ሐሳቦችን ከጽሑፍ ውስጥ መለየት፣ ለቃላት ፍቺ መስጠት፣ ወዘተ. መቻላቸውን የሚያረጋግጡ ዓይነት ናቸው (ግሩላንድ፣ 1976፤ አበበ 1990፣፣ችዱክ 2008፣ ቨሬቪጉና ሌሎች 2010፣ ታንግሰኩልና ሌሎች 2017):: በተማሪዎች በግንዛቤ ደረጃ እንዲዳብሩ የሚጠበቁ የትምህርት ዓላማዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚሰራባቸው የተለመዱ ቃላት/ግሶችም አነፃፅሩ፣ አስፋፉ፣ ለዩ፣ አስረዱ፣ በራሳችሁ አባባል ግለፁ፣ ምሳሌ(ዎች) ስጡ፣ እንደገና ጻፉ፣ ተንብዩ የሚሉትና የመሳሰሉት ናቸው (አበበ 1990፤ ግሩላንድ 1976፤ሳክስ፣ 1974፤)፡፡

## ሐ. ትግበራ/ መተግበር (Application/Applying) ትግበራ ተማሪዎች የተማሯቸውን ዘዴዎች፣ ፅንሰ ሀሳቦችና መርሆዎች፣ ህጎችና ቲዎሪዎች በሌላ አዳዲስ ሁኔታዎች

መጠቀም የመቻል አቅምን/ወይም ችሎታን/ ደረጃን ማዳበርን የሚመለከት ነው፡፡ ከግንዛቤ ከፍ ያለ ችሎታን የሚያመለክት የመማር ውጤት ነው (ግሩላንድ 1976፤ አበበ 1990፣፣ችዱክ 2008፣ ቨሬቪጉና ሌሎች 2010 ፣ ታንግሰኩልና ሌሎች 2017)፡፡ በዚህ ደረጃ የሚጠየቁት ጥያቄዎችም ተማሪዎች ጽንሰ ሀሳቦችንና መርሆዎችን በአዳዲስ ነባራዊ ሁኔታዎች ላይ እንዲተገብሩ ወይም መተግበር መቻላቸውን፣ ህጎችንና ቲዎሪዎችን በአዳዲስ ሁኔታዎች ላይ እንዲጠቀሙ ወይም መጠቀም መቻላቸውን፣ ችግሮችን (problems) እንዲፈቱ ወይም መፍታት መቻላቸውን፣ ቻርቶችንና ግራፎችን እንዲሰሩ ወይም መስራት መቻላቸውን፣ የተለያዩ ዘዴዎችን ትክክለኛ አጠቃቀም ሰርተው እንዲያሳዩ ወይም መስራት መቻላቸውን የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ይጠበቃል (ራኒ እና ሌሎች፣ 2004)፡፡ በትግበራ ክፍል የሚያገለግሉ የተለመዱ ቃላት ደግሞ ቀይሩ፣ አስሉ፣ ፈልጋችሁ አግኙ፣ አቃኑ፣ አዘጋጁ፣ ሰርታችሁ አሳዩ፣ ተጠቀሙ የሚሉትና የመሳሰሉት ናቸው (ግሩላንድ 1976፤ ሳክስ. 1974፤ አበበ 1990፣ ሙንዘንሜየር እና ሩቢን 2013)፡፡

## መ. ትንተና/መተንተን (Analysis/ Analyzing)

ትንተና/ መተንተን ከግንዛቤና ከትግበራ ከፍ ያለ አዕምሯዊ ችሎታ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ይዘትና የአወቃቀር ቅርጽ በአግባቡ መረዳት፣ እውነታዎችን/ መረጃዎችን መመርመር፣ የአንድን ሙሉ ማቴሪያል ለምሳሌ ጽሑፍ አላባዎች (components) መለየት፣ መከፋፈል እንዲሁም በክፍሎቹ መካከል ያሉትን ግንኙነቶች መተንተንና ግንኙነቶቹ የተመሰረቱባቸውን መሰረታዊ መርሆዎች መገንዘብ መቻል ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህ ችሎታዎች ደግሞ ነገሮችን በጥልቀት መረዳትንና ማገናዘብን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ይህም ትንተና ከፍተኛ የማገናዘብ/ የማሰብ ደረጃን የሚወክል ችሎታ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከቀዳሚዎቹ

ከግንዛቤና ከትግበራ ላቅ ያለ አዕምሯዊ ችሎታ ነው (አበበ 1990፤ ግሩላንድ 1976፤ ራኒ እና ሌሎች፣ 2004፤ ችዱክ 2008፣ ሽሬቪ.ጉና ሌሎች 2010፣ ታንግሰኩልና ሌሎች 2017፣ ሙንዘንሜይ እና ሩቢን፣ 2013)። በትንተና ክፍል ደረጃ የሚቀርቡ ጥያቄዎችም የተማሪውን በግልፅ ያልቀረቡ ሀሳቦችን መረዳት፣ ተጠየቃዊ (logical) የሆኑና ያልሆኑ ሀሳቦችን /ምክንያቶችን መገንዘብ፣ እውነታዎችን ከአንድምታዎች

(inferences) መለየት፣ የመረጃዎችን ተገቢነት መመርመር፣ የአንድን ስራ ለምሳሌ ጽሑፍን መዋቅር፣ አደረጃጀት፣ ወዘተ መተንተን፣ ውስጣዊ አወቃቀርን መፈለግ፣ ገፋፊ ምክንያቶችን መለየት፣ የአንድን ነገር አላባዎች (elements) መለየትና መከፋፈል መቻል የሚጠይቁ ናቸው (አበበ 1990፤ ግሩላንድ 1976)። በትንተና ክፍል ብዙ ጊዜ የሚሰራባቸው ቁልፍ ቃላትም ተንትኑ፣ ከፋፍሉ፣ ለዩ፣ አንድምታውን ግለፁ፣ ቢ.ጋር ንደፉ፣ አመልክቱ፣ አዛምዱ፣ በየክፍላቸው መድቡ የሚሉትና የመሳሰሉት ናቸው (ግሩላንድ 1976፤ ሳክስ፣ 1974፤ ራኒi እና ሌሎች 2004፤ሙለ እና ዳንኤል፣ 200፤ ሙንዘንሜየር እና ሩቢን፣ 2013)።

### ሠ. ቅንበራ /ማቀናበር (Synthesis)

:ቅንበራ" የፈጠራ ባሕርያትን በማዳበር ላይ የሚያተኩር አዕምሯዊ ችሎታ ነው። በመሆኑም በከፍተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታነት ይገለፃል። አዳዲስ ንድፎችን፣ አደረጃጀቶችን፣ ዕቅዶችን ወዘተ መቀመር በቅንበራ ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው የትምህርት ዓላማዎች ናቸው። ስለዚህ ቅንበራ ከትንተና በተለየ መልኩ አዲስና ሙሉ ነገር ለማዋቀር /ለመስራት፣ የአንድን ነገር ወይም ጉዳይ የተለያዩ ክፍሎች አቀናጅቶ ወደ አንድ ሙሉ ነገር ማምጣትን፣ የተፈታቱ ነገሮችን መልሶ መግጠምን (መገንባትን)፣ ማዋቀርን፣ አዳዲስ ተግባቦትን ለምሳሌ የንግግር ጭብጥ ወዘተ ማፍለቅን፣ ምርምር ማካሄድን፣ የምርምር ንድፍ ማዘጋጀትን፣ ወዘተ ተማሪዎች የሚለማመዱበት የአዕምሯዊ ትምህርት ክፍል ነው (አበበ 1990፤ ግሩላንድ፣ 1976፤ ራኒ እና ሌሎች፣ 2004፤ ችዱክ 2008፣ ሽሬቪ.ጉና ሌሎች 2010 ፣ ታንግሰኩልና ሌሎች 2017)።

በአጠቃላይ በዚህ በነብሉም አዕምሯዊ ምድብ በአምስተኛ ደረጃነት በቀረበው ቅንበራ በሚባለው ክፍል ከተማሪው ተጠባቂ የመማር ውጤቶች (learning outcomes) ትኩረት፣ ከዕውቀት እስከ ትንተና ባሉት ደረጃዎች ያዳበሯቸውን ችሎታዎች መሰረት በማድረግ የፈጠራ ባህርያትን በተለይም አዳዲስ ንድፎችንና አወቃቀሮችን፣ አዳዲስ ሐሳቦችን፣ ወዘተ. የማመንጨት፣ ዕቅድ የመንደፍና የመሳሰሉትን ችሎታዎች ናቸው (ራኒ እና ሌሎች፣ 2004፤)። ይህም የቅንበራ ደረጃ ከቀዳሚዎቹ ጋር ሲነፃፀር ውስብስብነቱ ላቅ ያለ/ ጠለቅ ያለ የማመዛዘንና የመፍጠር ችሎታን የሚጠይቅ እንደሆነ ያሳያል። በአዲስ መንገድ አዲስ ነገር በሚፈጠርበትና በሚዋቀርበት በዚህ ቅንበራ በሚባለው አዕምሯዊ ደረጃ የሚጠየቁ ጥያቄዎችም አዛምዱ፣ አሳጥሩ፣ ቀንሱ፣ አስፋፉ፣ መስርቱ፣ ተንብዩ፣ ድርሰት ጻፉ፣ አዲስ ሀሳብ አቅርቡ፣ ገንቡ (construct)፣ ፍጠሩ፣ ንደፉ፣ ለ... ችግሮች መፍትሄ አቅርቡ፣ አብራሩ፣ ፈትኑ (test)፣ አሻሽሉ፣ የተደራጀ ንግግር አድርጉ፣ አጭር ልቦለድ ወይም ግጥም ፈጥራችሁ ጻፉ፣ እቅድ አቅርቡ፣ የሚሉትና የመሳሰሉት ናቸው። በዚህ ክፍል የሚያገለግሉ መሰረታዊ (ቁልፍ) ቃላትም አቀናጁ፣ ከፋፍሉ፣ አሚሉ፣ ድርሰት ጻፉ፣ ፍጠሩ፣ ቀይሱ (ተልሙ)፣ ንደፉ፣ አብራሩ፣ እንደገና አዋቅሩ፣ እንደገና አደራጁ፣ ከልሱ፣ ጭመቁ፣ ተናገሩ የሚሉት ናቸው (ግሩላንድ፣ 1976፤ አበበ 1990፤ ሙንዘንሜየር እና ሩቢን፣ 2013፣ ችዱክ 2008፣ ሽሬቪ.ጉና ሌሎች 2010፣ ታንግሰኩልና ሌሎች 2017)።

### ረ. ግምገማ/መገምገም (Evaluation/ Evaluating)

በነብሉም ደረጃ አሰጣጥ ከፍተኛውና የመጨረሻው አዕምሯዊ ደረጃ /ችሎታ ግምገማ ነው። ለዚህ ችሎታ መገንባት ቀደም ሲል የቀረቡት አምስቱ አዕምሯዊ የችሎታ ክፍሎች በቅድመ ተከዋኝነት

(prerequisite) ያገለግላሉ። ግምገማ ማለትም ጥቅል በሆነ አገላለፅ የአንድን ማቴሪያል /ጉዳይ ለምሳሌ ልቦለድ፣ ግጥም፣ የምርምር ሪፖርት፣ ሀሳብ ወይም ሌላ ነገር ለሆነ ዓላማ የመመርመርና አዎንታዊ /

አሉታዊ ገፅታው ላይ ዳኝነት /ፍርድ ወይም ሀሳብ የመስጠት ችሎታ ነው፡፡ የማቴሪያሉን ወይም የጉዳዩን ወይም የሀሳቡን ጠቃሚ መሆን አለመሆን በተመለከተ ዳኝነት/ ፍርድ ወይም ሚዛናዊ የሆነ ሀሳብ ወይም ውሳኔ ለመስጠትም ግልፅ የሆኑ መስፈርቶችን መጠቀምን ግድ ይላል፡፡ መስፈርቶቹም ውስጣዊ ለምሳሌ የማቴሪያሉን አደረጃጀት፣ ወይም ውጫዊ ለምሳሌ ከዓላማው ጋር ያለውን ተገቢነት (relevance) መጠቀም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ መስፈርቶቹ በራሳቸው በተማሪዎቹ የተወሰኑ ወይም ከውጭ በሌላ ክፍል ለተማሪዎች የተሰጡ ሊሆኑ ይችላሉ (ግሩላንድ፣ 1976፤ ሳክስ፣ 1974፤ አበበ 1990፣ ችዱክ 2008፣ ሸሬቪጉና ሌሎች 2010 ፣ ታንግሰኩልና ሌሎች 2017)፡፡

ስለዚህ ተማሪው በተወሰነ መለኪያ መስፈርትነት አንድን ሐሳብ ወይም ሌላ ጉዳይ በጥልቀት በመመርመር እንዲገመግም ወይም እንዲሄስ ወይም ዳኝነት/ ፍርድ እንዲሰጥ፣ ወይም ሚዛናዊ የሆነ የውሳኔ ሐሳብ እንዲያቀርብ፣ ወዘተ የሚያዙ ተግባሮች በዚህ በግምገማ የትምህርት ዓላማ ስር የሚካተቱ ናቸው ማለት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ተማሪው የአንድን ማቴሪያል ለምሳሌ ጽሑፍ ተጠየቃዊ አደረጃጀት፣ የአንድን ማጠቃለያ በቂነት ወዘተ የተወሰኑ መስፈርቶችን ተጠቅሞ ዳኝነት ወይም ሀሳብ ወይም አስተያየት እንዲሰጥ ወይም ውሳኔ ላይ እንዲደርስ የሚያዙ ጥያቄዎች በዚህ አዕምሯዊ የትምህርት ዓላማ ስር ይካተታሉ (አበበ 1990፤ ግሩላንድ፣ 1976)፡፡ በዚህ ክፍል በቁልፍ ቃልነት የሚታወቁትም አወዳድሩ፣ ገምግሙ፣ አጠቃሉ፣ አነፃፅሩ፣ ተቹ፣ ምክንያት ስጡ (justify)፣ ተርጉሙ፣ አዛምዱ፣ አጠቃሉ፣ ድጋፋችሁን (ተቃውሚችሁን) አስረዱ፣ መስፈርት አውጡ፣ ደረጃ ስጡ፣ መዝኑ (assess)፣ ቅደም ተከተል ስጡ (በቅደም ተከተል አደራጁ)፣ ጠቀሜታቸውን አሳዩ የሚሉት ናቸው (ሙንዘንሜር እና ሩቢን፣ 2013፤ ሙለና ዳንኤል፣ 2005፤ ግሩላንድ፣ 1976) ፡፡

## ዝቅተኛና ከፍተኛ የአዕምሯዊ ችሎታ ደረጃዎች

አንዳንድ ተመራማሪዎች ደግሞ (ለምሳሌ ሳዲክ 2010፣ ችዲክ 2008) እነዚህን ስድስት የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች እንደገና ዝቅተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታዎችና ከፍተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታዎች በማለት በሁለት ክፍል ይመድቧቸዋል፡፡ በዝቅተኛ ደረጃነት የተመደቡት የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ማለትም እውቀትና ግንዛቤ የተባሉት አዕምሯዊ ችሎታዎች ሲሆኑ በከፍተኛ አዕምሯዊ ችሎታነት የተመደቡት ደግሞ ከትግበራ እስከ ግምገማ ያሉት አራቱ ክፍሎች/ ምድቦች ናቸው፡፡ ዝርዝር መገለጫቸው በቀዳሚዎቹ ክፍሎች ቀርቧል፡ ፡ በዚሁ መሰረት ከላይ የቀረቡት ስድስት የአዕምሯዊ ምድብ ችሎታዎች እንደገና ከዝቅተኛ ደረጃና ከከፍተኛ ደረጃ የአዕምሯዊ ምድብ ችሎታዎች አንጻር የኢትዮጵያ ፪ኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን በሁለቱ ደረጃዎች በመከፋፈል በምን ያህል ደረጃ እንደሚወከሉ መመርመር የዚህ ጥናት ሁለተኛው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚያ በፊት ግን ቀደም ብሎ እንደተጠቆመው እነዚህ የአዕምሯዊ ችሎታ ክፍሎች በሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት የተሰጣቸውን ቦታ በደምሳሳውም(ዝርዝር ውስጥ ሳይገባ) ቢሆን መመልከት ያስፈልጋል፡፡

ከፖሊሲው ለመነሳት ያህል፣ በ1986 ዓ.ም (እ.ኢ..አ.) በወጣውና እስካሁን እየተሰራበት ባለው አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ ውስጥ አምስት አጠቃላይ ዓላማዎች ተካተዋል፡፡ ከእነዚህ አምስት ዓላማዎች በፖሊሲው በተራ ቁጥር 2.1.2. ላይ የቀረበው ይበልጥ ክሂሎታዊ (psychomotor) ምድብ ላይ ያተኮረ ሲሆን ከአዕምሯዊ ምድብ ትግበራ አብሮ ተካቷል፡፡ 2.1.3 ደግሞ ስሜታዊ/አመለካከታዊ (affective) ምድብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የቀሩት ሦስት ዓላማዎች አዕምሯዊ ምድብ ስር በሚካተቱት አምስት ችሎታዎች ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ይህም በሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት ለአዕምሯዊ ምድብ የተለየ ትኩረት እንደተሰጠ የሚያመላክት ነው፡፡ እነዚህ ሦስት ዓላማዎችም የሚከተሉት ናቸው፤

አንደኛ በ2.1.1 ስር የሰፈረው “… የግለሰብን፣ የአካልና የአዕምሮ ተሰጥዖ በማጎልበት፣ የሚያጋጥሙ

ችግሮችን የማወቅና የመፍታት… ችሎታ ያዳበሩ ዜጎች ማፍራት”፤

ሁለተኛ በ2.1.4 የቀረበው “ የማመዛዘን፣ የመፍጠርና የመመርመር ችሎታን ማዳበር…”፣ ሦስተኛ በ2.1.5 የቀረበው “…አካባቢያቸውን የማወቅ፣ የማጤንና የመገንዘብ፣ የመመዘንና የመገምገም፣ የመተንተንና የመለወጥ… ችሎታ ያላቸው ዜጎች ማፍራት”፤ የሚሉ ናቸው። ሦስቱም ዓላማዎች የአዕምሯዊ የትምህርት ምድብን የተለያዩ የችሎታ ደረጃዎች ማዳበርን የሚመለከቱ ናቸው።

በእነዚህ ዓላማዎች ውስጥ የተካተቱ ቁልፍ ቃላትና ቃላቱን ያጀቧቸው ሀረጎች በግልፅ እንደሚያሳዩት በ2.1.1፣ በ2.1.4.

እና በ2.1.5. በቀረቡት አጠቃላይ ዓላማዎች ከትግበራ በስተቀር ሁሉም የአዕምሯዊ ምድብ ችሎታዎች ተካተዋል። ለምሳሌ ዕውቀት የሚባለው የመጀመሪያውና ዝቅተኛው የአዕምሯዊ ችሎታ ደረጃ በዓላማ 2.1.1 “… ችግሮችን ማወቅ” እና በ2.1.5 “… አካባቢያቸውን ማወቅ” በሚሉት ሀረጎች ተገልጿል። ሁለተኛው፣ የአዕምሯዊ ምድብ ችሎታ ግንዛቤ ሲሆን በፖሊሲው ዓላማ 2.1.5 “. … አካባቢያቸውን … የማጤንና የመገንዘብ… ችሎታ ያላቸው ዜጎች ማፍራት” በሚለው ሀረግ ውስጥ

“ማጤንና መገንዘብ” በሚሉት ቁልፍ ቃላት ተገልጿል። በዚህ አዕምሯዊ ምድብ በአራተኛ ደረጃነትና ከፍተኛ (ውስብስብ) ችሎታነት የሚታወቀው ትንተና ደግሞ በዓላማ

ቁጥር2.1.4. “የማመዛዘን…የመመራመር ችሎታን ማዳበር” እና በ2.1.5. ‹‹አካባቢያቸውን… የማጤን፣ የመገንዘብ፣

የመመዘን፣ የመተንተን ችሎታ ያላቸውን ዜጎች ማፍራት” በሚሉት ውስጥ ደምቀው (Bold ተደርገው) በተጻፉት ቃላት ተመልክቷል። አምስተኛውና በከፍተኛ አዕምሯዊ ችሎታነት ከሚታወቁት አንዱ የሆነው ቅንበራም እንዲሁ በፖሊሲው ዓላማ ቁጥር 2.1.1 “… “የሚያጋጥሙ ችግሮችን… የመፍታት ችሎታ ያዳበሩ ዜጎችን ማፍራት›” በሚል፣ በ2.1.4 .“የመፍጠርና የመመራመር ችሎታን ማዳበር፣” በ 2.1.5. “አካባቢያቸውን… የመለወጥ ችሎታ ያላቸው ዜጎችን ማፍራት” በሚሉት ውስጥ ደምቀው በተጻፉት ቃላት ተገልጿል። የመጨረሻውና በስድስተኛ የአዕምሯዊ ችሎታነት የሚታወቀው ግምገማ ደግሞ በፖሊሲው አጠቃላይ ዓላማ 2.1.5. “ …አካባቢያቸውን … የመመዘንና የመገምገም… ችሎታ ያላቸው ዜጎች ማፍራት” በሚለው ውስጥ የመመዘንና የመገምገም ችሎታ በሚሉት ቃላት ተገልጿል።

ሁለተኛው የሀገሪቱ መሰረታዊ የትምህርት ሰነድ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውን ለማስተግበር በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀው የኢትዮጵያ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ ነው። ከአፀደሕፃናት እስከ 12ኛ ክፍል የሚሰጠው ትምህርት የሚከተላቸውን መርሆዎች (prinicples)፣ እሴቶች (values)፣ ቁልፍ ብቃቶች (competencies) እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች የያዘ ሰነድ ነው። ቁልፍ ብቃቶች በሚለው ክፍል ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች አንዱና ዋናው በብሉምና ባልደረቦቻቸው (1956) ስራ የቀረቡት የአዕምሯዊ ምድብ (cognitive domain) ክፍሎች ናቸው። በዚህ ቁልፍ ብቃቶች በሚለው ክፍል በሕይወት ክሂሎት (life skills) ጀምሮ በጊዜ አጠቃቀም (Time Management) የሚቋጩ ሰባት ቁልፍ ብቃቶች (competencies) የተካተቱ ሲሆን የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች በየብቃቱ ተቀላቅለው እንዲቀርቡ ከመደረጉ በተጨማሪ ሦስተኛውና ከፍተኛ-ደረጃየማሰብ ችሎታ (Higher-Order-Thinking) የሚለው ሙሉ በሙሉ በዚህ አዕምሯዊ ምድብ ስር የሚካተቱ ክፍሎችን ብቻ የያዘ ነው። በዚህ ክፍል ከአዕምሯዊ ችሎታዎች ትኩረት የተሰጠውም ከፍተኛ ደረጃ ለሚባሉት አዕምሯዊ ችሎታዎች ማለትም ለትግበራ፣ ለትንተና፣ ለቅንበራና ለግምገማ ነው። በቁልፍ

ብቃትነት ከቀረቡት ሰባት ክፍሎች በሦስተኛ ደረጃ ላይ በቀረበው ከፍተኛ-ደረጃየማሰብ ችሎታ የሚለው ስር ሁለት ክፍሎች የተካተቱ ሲሆን የመጀመሪያው ሥርዓተ ትምህርቱ እውቀትን ተግባራዊ የማድረግ ችሎታን በሚያዳብር፣ ትንተናን፣ ቅንበራን፣ ግምገማንና አዳዲስ አሰራርን በሚያሳድግ መንገድ ሊቀርብ እንደሚገባው አቅጣጫ የሚያሳይ ነው።

ሁለተኛው ተማሪዎች ችግሮችን በመፍታት ዐውድ ጠለቅ (ላቅ ያለ) አስተሳሰብንና አዳዲስ ነገሮችን የማመንጨት (የፈጠራ) ክሂሎችን (Critical Thinking and Creative Thinking Skills) ማዳበር እንደሚኖርባቸው የተገለፀበት ክፍል ነው። በሁለቱም ክፍሎች የተገለፁት ሀሳቦች የሀገሪቱ ትምህርት ከፍተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታዎችን ማዳበር ላይ ሊያተኩር እንደሚገባው የሚያሳስቡ/ የሚያስገነዝቡ ናቸው። የዚህም አንድምታ በሀገሪቱ ትምህርት ቤቶች በየትምህርት ዓይነቶቹ የሚሰጠው ትምህርት ለአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች በተለይም ለከፍተኛ ደረጃ ችሎታዎች ከፍተኛ ትኩረት የሰጠ ሊሆን እንደሚገባው የሚያመለክት ነው። በቂ እርሾ (መሰረታዊ ችሎታ) ይዘው ለሚመጡ ተማሪዎች የሚሰጥ የአፍ መፍቻና የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ደግሞ ይህን የማድረግ የበለጠ ግዴታ ይኖርበታል። ከሕይወት ክሂሎት ጀምሮ በሥርዓተ ትምህርቶቹ እንዲዳብሩ የተካተቱት አብዛኞቹ ብቃቶች (Comptencies) በጥልቀት ሲታዩ በቋንቋ ትምህርቶች ሊዳብሩ የሚችሉ ብቃቶች ናቸው። የትምህርት ዓላማዎች ከግብ መድረስ አለመድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚዘጋጁ የክፍልም ሆነ ብሔራዊ ፈተናዎችም የዚህ ነፀብራቅ መሆን ይጠበቅባቸዋል (Hughes, 2003)።

ይህም እነዚህ በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውና በሥርዓተ ትምህርት ማስፈጸሚያ ሰነዱ የተካተቱ የአዕምሯዊ ምድብ  ዓላማዎች በአጠቃላይ ፪ኛደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተናዎች በአግባቡ ሊወከሉ እንደሚገባቸው የሚያሳይ ነው።

የዚህ ጥናት አንደኛው ትኩረትም እነዚህ ስድስት ደረጃዎች በፈተናዎቹ በተገቢ ናሙና የሚሸፈኑ / የሚወከሉ መሆን አለመሆናቸውንና አወካከላቸው በብሉም እና በሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ ሰነዶች በተሰጣቸው ትኩረት መሰረት አዎንታዊ የመማር ማስተማር ሂደትን ለማበረታታት በሚያስችል መልኩ መሆን አለመሆኑን መመርመር እንዲሆን ያደረገው አንዱ ምክንያት ይኸው ነው። በሚመዘነው/ ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ምድቦች (Target Language Domains) እና በፈተና የሚካተቱ ችሎታዎች መካከል ተጣጥሞሽ (Overlaping)ሊኖር እንደሚገባው የሚገልጸው የግሪን(2007) የወሸባክ ሞዴልም ይህንኑ የሚያበረታታ ነው። የፈተና ተጽዕኖ በኦልደርሰን (1999) ሥራ አጽንኦት አግኝቶ እንደቀረበው በተለይ የፈተናው ዋነኛ ዓላማ የተማሪዎችን ችሎታ መለካት ከሆነ፣ በማስተማር መማር ሂደቶች ላይ የሚያሳድሩትን አዎንታዊ ተጽዕኖ ከፍ  ለማድረግ ፈተናዎቹ በተቻለ መጠን ከሥርዓተ ትምህርቱና ከክፍል ትምህርቱ ጋር የሚዛመዱ ወይም የሥርዓተ ትምህርቱና የክፍል ትምህርቱ ነጸብራቅ ሊሆኑና የመማር-ማስተማሩ ሂደት ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊሳድሩ የሚችሉ አይነት ሊሆኑ ይገባቸዋል። የተማሪዎችን ችሎታ ለመለካት እና / ወይም ወደቀጣዩ የትምህርት ደረጃ የሚሻገሩ ተማሪዎችን  ለመለየት የሚዘጋጁ ፈተናዎች አዎንታዊ ትርጉም እንዲኖራቸውም ሲዘጋጁ ከሥርዓተ ትምህርቱና ቀደም ብለው ከቀረቡት የትምህርት  አጠቃላይ ዓላማዎቹ ጋ እንዲጣጣሙ/ ተገቢ ተዛምዶ እንዲኖራቸው ማድረግን ይጠይቃል። ሌላው ቀርቶ የብቃት መለኪያ (Proficiency) ፈተና እንኳ ቢሆን መምህራኑ ካስተማሩት/ተማሪዎቹ ከተማሩት ትምህርት ጋር መሰረታዊ ልዩነት (Major Mismatch) እንዳይታይበት ጥንቃቄ መደረግ አለበት የሚለው የኦልደርሰን( 1999) አገላለጽም የፈተናዎች ኤጅንሲ ሃላፊዎችን ሀሳቦች የሚያጠናክር ነው። እነዚህ ሀሳቦች አንድ ፈተና በተለይም ውጫዊ/ብሄራዊ ፈተና ከትምህርት በተለይም ከፍተኛ ደረጃ ከሚባሉት አዕምሯዊ ምድብ ዓላማዎች ያፈነገጠ ከሆነ የታለመው ትምህርት ግቡን እንዳይመታ የሚያደርግ አሉታዊ ሚና ሊጫወት እንደሚችል የሚያመለክቱ ናቸው። በተቃራኒው በኦልደርሰንና  ዎል(1993)፣ ችንግ (1997)፣ ሾኃሚንና ሌሎች (1996) ጥናቶች እንደተረጋገጠው አንድ ፈተና እንዲመዝን የሚጠበቅበትን  የሚመዝን ከሆነ  ደግሞ

ጥሩ ማስተማርንና መማርን ሊያበረታታ ይችላል። ለምሳሌ የሹሃሚና ሌሎች (1996)) ጥናት ጥሩ ፈተና በትምህርት ይዘትና የማስተማሪያ ዘዴ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል አሳይቷል። የዚህ ጥናት ሌላው ዓላማም ከዚህ አስተሳሰብ አንጻር የየኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተናዎች ምን ያህል ጥሩ መማርን እያበረታቱ ነው? የሚለውን መፈተሽ ነው።

በተጠቀሰው ርዕስ ጥናት ለማካሄድ ዋነኛ መነሻ ችግር/ አነሳሽ ምክንያት የሆነው በኢትዮጵያ፣ በአዲሱ አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ (1986) መሰረት የ፪ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና ከ1993 (እ.ኢ.አ.) ጀምሮ ከ12ኛ ክፍል ወደ 10ኛ ክፍል ዝቅ እንዲል ተደርጓል (ውብሸት 1992)። ከ1993 ጀምሮ እስካሁን ያሉት ጊዜያት ረጅም ናቸው። ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ቤተ መጻሕፍት በተደረገው ፍተሻ ከ1950ዎቹ- እስካሁን በዚህ ጉዳይ ላይ የተካሄዱ ጥናቶችን ለመፈተሽ በተደረገው ጥረት በፈተና ላይ ስድስት ለመጀመሪያ ዲግሪና ሁለት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተሰሩ ጥናቶች ማግኘት ቢቻልም አንዳቸውም በዚህ ጥናት ከተጠቀሰው ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሆነው አልተገኙም። በሌላ አባባል አንዳቸውም በአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎችና በፈተናዎቹ መካከል ስላለው ዝምድና የሚያነሱት ነገር የለም። ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ ደረጃ ግንኙነት ያለው ሆኖ የተገኘው በ1998ና በ1999 ዓ.ም (እ.ኢ.አ.) የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተናዎች ላይ ተመስርቶ በባህርዳር ዩንቨርሲቲ፣ በአበባ (2000) (እ.ኢ.አ.) የ10ኛ ክፍል አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና በመማር-ማስተማር ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተሰራው የመመረቂያ ጥናት ብቻ ነው። ይህም ጥናት ቢሆን ትኩረቱን ከመማሪያ መጽሐፉ ይዘት ተዛምዶ ላይ ያደረገ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያለው ቢመስልም በፈተናዎቹና በሀገሪቱ የፖሊሲ ሰነዶች ከፍተኛ ትኩረት ስለተሰጣቸው የአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች ያነሳው ምንም ነገር ስለሌለ ከዚህኛው ጥናት ይለያል ። በመሆኑም በተጠቀሰው ርዕስ ጥናት ለማካሄድ የተፈለገው ከላይ በተጠቀሱት የፈተና ምሁራን እንደተገለጸው በኢትዮጵያ ዐውድ የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ የብሎም አዕምሯዊ ምድብ ዓላማዎችና የትምህርት ፖሊሲው ሰነዶች ነጸብራቅ ስለመሆን አለመሆናቸው የሚያሳይ ጥናት ስላልተካሄደና በቂ መረጃ ስለሌለ ይህን ክፍተት ለመሙላት ነው። ሁለተኛው ምክንያት በትምህርት ፖሊሲው መሰረት አማርኛ አፍ መፍቻቸው የሆኑትም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው ያላቸው ችሎታ ከጊዜ ጊዜ ደካማ እየሆነ መጥቷል፣ የሚለው አተያይ በጥናቶችም እየተደገፈ ስለመጣ የዚህ አንዱ መንስዔ ፈተናዎቹ የሚያሳድሩት አሉታዊ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል የሚለው አተያይ ነው።

በዚሁ መሰረት የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች ጋ ያለውን ተጣጥሞሽ/ግንኙነት ፣ ከፍተኛ የአዕምሯዊ ምድብ የሚባሉ ዓላማዎች ውክልና እና በፈተናዎቹ የዓላማዎቹ ውክልና በመማር ማስተማሩ ሂደቶች ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተጽዕኖ መመርመር ሲሆን ዝርዝር የምረምር ጥያቄዎች ደግሞ፤ አንደኛ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ባህርያዊ ዓላማ ክፍሎች/ ችሎታዎች ጋር ይጣጣማል? ሁለተኛ የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና ከፍተኛ የአዕምሯዊ ምድብ ዓላማዎች (ትግበራ፣ ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ) ትኩረት እንዲያገኙ የሚያበረታታ ነው? ሦስተኛ ማጠናቀቂያ ፈተናው ከአዕምሯዊ ምድብ አንጻር በማስተማር-መማር ሂደቶች ላይ ሊያሳድረው የሚችለው ተጽዕኖ ምንድን ነው? የሚሉት ናቸው።

## የአጠናን ዘዴ

የጥናቱ ንድፍ ገላጭ ተዛምዷዊ ሆኖ ይዘት ትንተና(ሰነድ ፍተሻ ) እና ግምገማ ላይ ያተኮረ ነው። ለጥናቱ የመረጃ ምንጮች ሆነው የተወሰዱት ከ2002-2004 የተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ የ2ኛ ደረጃ የሦስት ተከታታይ

ዓመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች 270 ጥያቄዎች፣ ሁለት የፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና ሁለት የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ የመረጃ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን በተለይ ደግሞ የፈተናዎችን ጥያቄዎች ለመተንተንና በመማር ማስተማር ሂደቶቹ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ ለመመርመርም በክለሳው ክፍል የተገለጸው በብሉምና ሌሎች (1956) የዳበረውና በነአንደርሰን (2001) መጠነኛ ክለሳ የተደረገባቸው የብሉም አዕምሯዊ ምድብ ባሕሪያዊ የትምህርት ዓላማዎች በመገምገሚያ መስፈርትነት አገልግሏል፡፡

እንዲህ ያለ ከተጣጥሞሽ /ዝምድና ጋር የተያያዘ ጥናት ሲካሄድ የሚነሳው ጥያቄ በፈተናዎችና እንዲመዘኑ በሚፈለጉት ችሎታዎች/በዚህ ጥናት ዐውድ በአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች፣ መካከል ያለውን የግንኙነትና የግንኙነት ደረጃ እንዴት ባለ ያጠናን ሄደት ማጥናት ይቻላል? የሚለው ነው፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ሦስት ያጠናን ስልቶች እንዳሉ በኦልደርሰንና ሌሎች (1995) ስራ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከሦስቱ አንደኛው፣ በራሱ በአጥኚው የጥያቄዎችን ይዘት ከልየታዎቹ ወይም ከመርሐ ትምህርቱ(ቶቹ) ይዘቶች ጋር የማወደደር ስልት ነው(Compare test content with specifications/ syllabus):: ሁለተኛው መምህራን፣ በሙያው የላቀ ችሎታ ያላቸው ምሁራን… የሚሞሏቸው መጠይቆችና አስተያየታቸውን የሚገልፁባቸው ቃለመጠይቆችን ማዘጋጀት ነው፡፡ ሦስተኛው፣ በፈተናው ጥያቄዎች ላይ ባለሙያዎች ዳኝነት እንዲሰጡ_ የትኛው ጥያቄ የትኛውን ችሎታ እንደሚለካ እንዲገልፁ (Experts judgment) እድል የሚሰጠውና በልዩነታቸው ላይ (ከተከሰተ) እንዲወያዩ እድል የሚሰጠው ስልት ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አገልግሎት ላይ እየዋለ ያለውና በዌር እና ሌሎች (1990) ስራም ተመራጭ ዘዴ ሆኖ የቀረበው ሦስተኛው ስልት ነው፡ ፡ የታንጉስኩልና ሌሎች(2117) ጥናትም በዚሁ ስልት የተካሄደ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹና በአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ባህሪያዊ ዓላማዎች መካከል ያለውን ተዛምዶ ለማጥናት ዋነኛ ዘዴ ተደርጎ የተመረጠው ሦስተኛው ስልት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት እ..ኢ.አ. ከ2002-2004 ዓ.ም. ባለው ጊዜ

ሰንጠረዥ 1. የፈተና ጥያቄዎች ስርጭት ከአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች አንፃር የየዓመቱና የሦስቱ ዓመታት ጠቅላላ ድምር በቁጥርና በመቶኛ ስሌት

| የአዕምሯዊ ምድብ ደረጃዎች | ዓመተ ምሕረት 2002 | | 2003 | | 2004 | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| ዕውቀት/ ማስታወስ | 27 | 30 | 25 | 27.77 | 14 | 15.58 | 66 | 24.44 |
| ግንዛቤ/ መረዳት | 57 | 63.33 | 55 | 61.11 | 68 | 75.55 | 180 | 66.67 |
| ትግበራ/ መተግበር | 4 | 4.44 | 5 | 5.56 | 5 | 5.56 | 14 | 5.19 |
| ትንተና/ መተንተን | - | - | 5 | 5.56 | 2 | 2.22 | 7 | 2.59 |
| ቅንበራ/ ማቀናበር | 2 | 2.22 | - | - | 1 | 1.11 | 03 | 1.11 |
| ግምገማ/ መገምገም | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ድምር | 90 | 100 | 90 | 100 | 90 | 100 | 270 | 100 |

የተዘጋጁት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ጥያቄዎች ከአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጥናት በአራት ባለሙያዎች፣ ምደባው እንዲካሄድ ተደርጓል፡፡ ከእነዚህ አራት የሥነ-ትምህርት ባለሙያዎች መካከል ሁለቱ በሥርዓተ ትምህርትና ሥነ-ማስተማር፣ አንዱ አንዱ በምዘናና ግምገማ አራተኛው አማርኛን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ናቸው፡፡ የሦስቱ ባለሙያዎች መጀመሪያ ዲግሪ

ፔዳጎጂ ሲሆን የአንዱ አማርኛ ነው፡፡ አራቱም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህርነትና በጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በሌክቸረርነት ከ10 ዓመት በላይ ያገለገሉና ይህ ምድብ በትምህርትነት የሚሰጡ ኮርሶችን ያስተማሩ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሁለት የፈተናዎች ኤጀንሲ ኃላፊዎችና ከሁለት የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች በቃለ መጠይቅ ተጨማሪ መረጃ ተሰብስቧል፡፡

የተሰበሰቡት መረጃዎችም መጠናዊ የሆኑት በገላጭ ስታትስቲክስ በተለይም በድግግሞሽና በመቶኛ፣ ዓይነታዊ የሆኑት ደግሞ በጭብጣቸው መሰረት ተተንትነዋል፡፡ ከዚያም የውጤት ትንተናዎችን በተዛማጅ ድርሳንነት ከቀረቡት አተያዮች ጋ በማገናዘብ የማጠናቀቂያ ፈተናዎቹ ከአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች ጋ ያላቸው ግንኙነትና የከፍተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ምድብ ችሎታዎች ውክልና ምን እንደሚመስልና የፈተናው ዝግጅት በማስተማር መማር ሂደቶች ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖን ለማዳበር የሚረዳ መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል፡፡

## የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ ክፍል መጀመሪያ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ጥያቄዎች ከአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ባህርያዊ ዓላማ ክፍሎች/ ችሎታዎች ጋር ይጣጣማሉ? የሚለውን ጥያቄ በሚመለከት የተሰበሰቡት መረጃዎች የውጤት ትንተናና ማብራሪያ ይቀርባል፡፡ ከዚያም የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና ከፍተኛ የአዕምሯዊ ምድብ ዓላማዎች (ትግበራ፣ ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ) ትኩረት እንዲያገኙ የሚያበረታታ ነው? የሚለውን የሚመለከተው ክፍል ይከተላል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ፈተናዎቹ በመማር-ማስተማር ሂደቶች ላይ ሊያሳድሯቸው የሚችሏቸውን ተጽዕኖዎች የሚመለከተው ክፍል ይቀርባል፡፡

ሰንጠረዥ 2. የፈተናዎቹ ጥያቄዎች ስርጭት ከዝቅተኛና ከከፍተኛ አዕምሯዊ ምድብ ደረጃዎች አንፃር የየዓመቱና ጠቅላላ

| | ዓመተ ምህረት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአዕምሯዊ ምድብ ደረጃዎች | 2002 2003 2004 ድምር ብዛ ብዛ ብዛ ብዛ | | | | | | | |
| | ት | % | ት | % | ት | % | ት | % |
| ዝቅተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታዎች ምድብ (የዕውቀትና ግንዛቤ) ውክልና ድምር | 84 | 93.33 | 80 | 88.77 | 82 | 91.13 | 246 | 91.11 |
| የከፍተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ምድብ ችሎታዎች ውክልና | | | | | | | | |
| ሀ. ትግበራ (መተግበር) | 4 | 4.4 | 5 | 5.55 | 5 | 5.55 | 14 | 5.18 |
| ለ. ትንተና ( መተንተን) | - | - | 5 | 5.55 | 2 | 2.22 | 7 | 2.53 |
| ሐ. ቅንበራ ( ማቀናበር) | 2 | 2.2 | - | - | 1 | 1.11 | 3 | 1.11 |
| መ. ግምገማ (መገምገም) | - | - | - | - | - | - | - | - |
| የከፍተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታዎች ምድብ ውክልና ድምር | 6 | 6.6 | 10 | 11.10 | 8 | 7.88 | 24 | 8 89 |

## ሀ. የአዕምሯዊ ምድብ (Cognitive Domain) ክፍል ዓላማዎችና የማጠናቀቂያ ፈተናው ጥያቄዎች ተጣጥሞሽ

ይህ ክፍል የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ጥያቄዎች ከአዕምሯዊ ምድብ (Cognitive Domain) የትምህርት ባሕርያዊ ዓላማዎች ጋር ይዛመዳሉ? የሚለውን ጥያቄ በሚመለከት የተሰበሰበው መረጃ ተተንትኖና ተብራርቶ የቀረበበት ነው፡፡

በቀዳሚው ክፍል እንደተገለጸው፣ የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች የሚባሉት ዕውቀት፣ ግንዛቤ፣ ትግበራ፣ ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ በመባል የሚጠሩት የአዕምሯዊ ችሎታ ደረጃዎች ናቸው፡፡ ቀደም ባሉት ክፍሎች እንደተገለፀው አንድ ሀገር እነዚህን የአዕምሯዊ ምድብ ችሎታዎች ለማዳበር የሚያስችል የትምህርት ሥርዓት መዘርጋት ይጠበቅበታል፡፡ በኢትዮጵያም በፖሊሲና በፖሊሲ ማስፈፀሚያ ሰነድ ደረጃ እነዚህ ጉዳዮች ከፍተኛ ቦታ እንዳገኙ ተረጋግጧል፡፡

በፖሊሲ ሰነዶች ብቻ ሳይሆን በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማርና በምዘና ሂደቶች በተግባር ሲተገበሩ መታየትም ይኖርባቸዋል፡፡ ዓላማዎቹ በመማር-ማስተማርና በምዘና ሂደቶች የሚፈለጉት ለውጦች መምጣትና አለመምጣታቸው ከሚፈተሽባቸው መንገዶች አንዱና ዋናው ደግሞ በክፍልና በብሔራዊ ደረጃ የሚካሄዱ ምዘናዎችን በማጥናት ነው፡፡ በመሆኑም ይህን በሚመለከት በቅድሚያ ቀደም ብሎ እንደተወሳው ከፈተናዎች ኤጀንሲ ሃላፊዎች(ሀላፊ ፩ና ፪)እና ባለሙያዎች(ባለሙያ ፩ እና ፪ ) በቃለመጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ ውጤት ትንተና እንዳሳየውም በፈተናዎቹ ዝግጅት ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ የአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች ናቸው ፤ ለዚህም ለፈተና ዝግጅት ሃላፊዎችና ባለሙያዎች እንዲሁም ለየትምህርት አይነቶች የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች ፈተናዎቹ የብሉም አዕምሯዊ ምድብ ዓላማዎች ነጸብራቅ እንዲሆኑ የሚያግዙ (ከውጭ ሀገር በመጡ አሰልጣኞች ጭምር)ስልጠናዎች እንዲያገኙና ፈተናዎቻቸውን በዚሁ መሰረት እንዲያዘጋጁ ለማድረግ ጥረትና ክትትል ይደረጋል፡፡ ከስልጠናው በተጨማሪ የስርዓተ ትምህርቶቹ መሳሪያዎች፣ የፈተና አዘገጃጀት መርሆ ሰነዱንና የሚመዘኑ ክፍሎችን የያዙ የፈተና ዕቅዶችም (specifications) ለጥያቄ ፀሐፊዎች እንደሚሰጡ በውይይቶቹ ተገልጿል፡፡ ለምሳሌ ባለሙያ፪ ስለዚህ ጉዳይ በገለጹበት ክፍል ሲናገሩ "አዎ ምንድነው.. ፈተናው ሁሉንም የክሂል ዘርፎች እንደገና ደግሞ ሁሉንም የዕውቀት ዘርፎች (የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች) እንዲወክል ተደርጎ ነው የሚዘጋጀው" ሲሉ ሃላፊ፪ም ፈተናው ከተዘጋጀ በኋላ እያንዳንዱ የስርዓተ ትምህርት ዓላማ እንደሚቆጠር (ታሊ እንደሚደረግ)፣ በቆጠራውም የትኛው ዓላማ የትኛው የዕውቀት ክፍል (category) ላይ ፣ (የትኛው ዕውቀት ላይ፣

የትኛው መረዳት ላይ፣ የትኛው ትንተና ላይ… ) እንደሚያርፍ እንደሚፈተሽ ገልጸዋል፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በሳይኮሎጅ፣ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ደግሞ በትምህርት ምዘናና ፈተና (Educational Assessment and Examination) እንግሊዝ ሀገር የሰሩት ሀላፊ ፩ም "ጥያቄ ፀሐፊዎች የሚያዘጋጇቸው ጥያቄዎች በየትምህርት አይነቱ የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች የሚመረመሩትም በዚሁ የትኞቹ ጥያቄዎች መረዳትን፣ ትግበራን፣ ትንተናን… እንደወከሉ እየተጠና ነው፤" ብለዋል፡፡ ይህም በፈተናዎች ኤጀንሲ ሀላፊዎችና ባለሙያዎች ግንዛቤ በፈተናዎቹ ዝግጅት ሂደት ለአእምሯዊ ምድብ ትኩረት ይሰጣል የሚል ዕምነት እንዳለ ያሳያል፡፡ በተግባር ያለው ዕውነታ ደግሞ ቀጥሎ የፈተናዎቹ ጥያቄዎች ሲመረመሩ የሚነሳ ጉዳይ ይሆናል፡፡

በዚህ ረገድ በሰንጠረዥ 1. የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ግንዛቤ (መረዳት) 2002 ዓ.ም በ57 ጥያቄ (63.33%)፣ በ2003 በ55 ጥያቄ (61.11%) እና በ2004 ዓ.ም በ68 ጥያቄ (75.55%) በመወከል በሦስቱም ዓመታት የመጀመሪያውን የውክልና ደረጃ ይዟል፡፡ በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው እንደግንዛቤ

ሁሉ በሦስቱም ዓመታት በተመሳሳይ ሁኔታ በ2ኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ዕውቀት(ማስታወስ) ነው፡፡ ትግበራ በ2002 በ4.4% ፣ በ2003 እና በ2004 ዓ.ም በ5.55% በመወከል ከዕውቀት ያለው ርቀት ከፍተኛ ቢሆንም በፈተናዎቹ ውክልና በማግኘት በሦስተኛ ደረጃነት ይከተላል፡፡ ትንተና በ2003 ዓ.ም በአምስት ጥያቄ (5.5%)፣ በ2004 ደግሞ በሁለት ጥያቄ (2.2%) ሲወከል በ2002 ዓ.ም በአንድም ጥያቄ አልተወከለም፡፡ ቅንበራ ደግሞ በ2003 በሁለት ጥያቄ(2.2%) ፣በ2004 በአንድ ጥያቄ (1.11%) ተወክሏል፡፡ በ2003 ምንም ውክልና አላገኘም፡፡ ግምገማ በየትኛውም ዓመት ፈተና ውክልና ያላገኘ ምድብ ነው፡፡

የሦስቱ ዓመታት ድምርርና አማካይም ተመሳሳይ መልክ ይታይበታል፡፡ ማለትም ግንዛቤ በከፍተኛ የጥያቄ ቁጥር (66.67%) ሲወከል እውቀት በ24.44% በርቀት በሁለተኛ ደረጃነት ይከተላል፡፡ ትግበራ በ14 ጥያቄ በ5.14% ሦስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በሰባት ጥያቄ በ2.53% በመወከል በአራተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ደግሞ ትንተና ነው፡፡ ቅንበራ በሦስት ጥያቄ በ1.11% የመጨረሻውን ደረጃ ይዟል፡፡ በውስብስብነት ደረጃው ስድስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ግምገማ

በየትኛውም ዓመተ ምህረት ፈተና ጥያቄዎች በአንድም ጥያቄ መወከል ያልቻለ ዓላማ ነው፡፡ ከውጤት ትንተናው ማስተዋል እንደሚቻለው ግንዛቤና ዕውቀት የተሻለ ውክልና ሲያገኙ ግምገማ፣ ቅንበራና ትንተና ደግሞ በፈተናዎቹ ትኩረት ያላገኙ የአዕምሯዊ ምድብ ዓላማዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህም የፈተናዎቹ ዝግጅት በክለሳ ድርሳናትና በሀገሪቱ የፖሊሲ ሰነዶች መሰረት አለመሆኑንና ውክልናው ዘፈቀዳዊ የሚመስል እንደሆነ የሚጠቁም ነው፡፡

ይህም ግኝት አንደኛ የፈተናዎቹ ዝግጅት በክለሳ ድርሳንነት የቀረቡትን አስተሳሰቦች ግምት ውስጥ እንደማያስገባ ያመላክታል፡፡ ሁለተኛ የፈተናዎች ኤጀንሲ ባለሙያዎችና የአማርኛ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች የፈተናዎቹ ጥያቄዎች የብሉምን አዕምሯዊ ምድብ ዓላማዎች የሚያንጸባርቁ እንዲሆኑ ጥረት ይደረጋል ያሉትን ሀሳብ ይጻረራል፡፡ ሦስተኛ የሀገሪቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲና የሥርዓት ትምህርት ማስፈጸሚያ ማዕቀፉ ነጸብራቅ ሳይሆን ተገኝቷል፡፡ ምክንያቱ የፈተና አዘጋጆቹ በዚህ ረገድ ተገቢ አቅም ያዳበሩ አለመሆን ሊሆን ይችላል፡፡

### ለ. በአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና ከፍተኛ የአዕምሯዊ ምድብ ዓላማዎች (ትግበራ፣ ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ) ያገኙት ትኩረት

ሁለተኛው ጥያቄ የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና ከፍተኛ የአዕምሯዊ ምድብ ዓላማዎች (ትግበራ፣ ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ) ትኩረት እንዲያገኙ የሚያበረታታ ነው? የሚለው ነው፡፡ ይህን ጥያቄ በሚመለከት በሰንጠረዥ 2 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው ዝቅተኛና ከፍተኛ የአዕምሯዊ ችሎታ ደረጃ እየተባለ ከሚካሄደው በክለሳው ከቀረበው ባለሁለት ክፍል አመዳደብ አንፃር ሲታይ በዝቅተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታነት የሚመደቡት ዕውቀትና ግንዛቤ በ246 ጥያቄ ወይም በ91.11% ሲወከሉ በከፍተኛ የአዕምሯዊ ችሎታ ደረጃነት የሚመደቡት ትግበራ፣ ትንተናና ቅንበራ ደግሞ በ24 ጥያቄ (በ8.88%) ብቻ ተወክለዋል፡ ፡ ግምገማ በአንድም ጥያቄ አለመወከሉ ቀደም ብሎ ተገልጿል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና እነብሉም (1956) እንዲህ ያለውን በዝቅተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታ ላይ የሚያተኩር የፈተና ዝግጅት ችግር ለማስወገድ ያዳበሩትን የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች የሚፃረር ብቻ ሳይሆን ቀደም ብለው የተገለፁትን በሀገሪቱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና በሥርዓተ ትምህርት ማስፈጸሚያ ማዕቀፉ የተሰጡ የትኩረት አቅጣጫዎችን፣ ቁልፍ ብቃቶችን እንዲሁም በቋንቋው ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት የቀረቡ የትምህርቱ መሰረታዊ ዓላማዎችን በሚቃረን መንገድ እየተዘጋጀ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከፈተናዎች ኤጀንሲ ሁለት ኃላፊዎችና ሁለት የአማርኛ ቋንቋ ፈተና

ዝግጅት ባለሙያዎች ጋር በተካሄዱት ቃለመጠይቆችፈተናዎቹ ሲዘጋጁ ጥያቄዎቹ ከፍተኛ የአዕምሯዊ ምድብ ችሎታዎችን/ ዓላማዎችን ጨምሮ ለአዕምሯዊ ምድብ ትኩረት ይሰጣል ያሉትን ሀሳብ የሚጻረር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ረገድ በውይይቶቹ የጥያቄ አዘጋጆችንና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎችን አቅም ከፍ ለማድረግም/ለማጎልበትም የተለያዩ ከውጭ ሀገር በመጡ ባለሙያዎች ሳይቀር ስልጠናዎች እንዲሰጣቸው ይደረጋል የተባለ ቢሆንም የውጤት ትንተናው ግን የተባለውን የሚያንጸባርቅ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ከቀደምት ጥናቶች ጋር ሲገናዝብም ለምሳሌ በ9ኛ ክፍል ፈተና ላይ በዚሁ ጉዳይ የተሰራው የታንገሰኩልና ሌሎች (2017) ጥናት ለማስተዋስና ለመረዳት የተሻለ ትኩረት በመስጠት ከዚህ ጥናት ጋር የሚደጋገፍ ሲሆን በተወሰነ ደረጃ ክፍተኛ ደረጃ የአምሯዊ ምድብ የማሰብ ችሎታዎችን በመጠኑም ቢሆን በመመዘን የነታንሰኩል(2017) ጥናት ግኝት የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ ጥናት ግኝት ሁሉም ከፍተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታ (መተግበር፣ መተንተን፣ማቀናበርና መገምገም) የሚባሉት በብዙ ጥያቄዎች ከተወከሉበት የአብዱልጀባርና ኦማር (2015) ጥናት ይጻረራል፡፡ ከዚህም የፈተናው አዘገጃጀት ብዙ እንደሚቀረውና ፈተናውን የተሻለ ለማድረግ ገና ብዙ መሰራት እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፡

## ሐ. ፈተናዎቹ በመማር-ማስተማር ሂደቶች ላይ ሊያሳድሯቸው የሚችሏቸው ተጽዕኖዎች

ሦስተኛው ጥያቄ ከጥናቱ ውጤት በመነሳት የፈተናው አዘገጃጀት ምን ያህል ጥሩ/ አዎንታዊ ማስተማር መማር ሂደቶችን ሊያበረታታ ይችላል? የሚለው ነው፡፡ ይህን የምርምር ጥያቄ በሚመለከት የተገኘው ምላሽም በኤጀንሲው በየዓመቱ እየተዘጋጁ ያሉት የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ/ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች በመማር-ማስተማሩ ሂደት መምህራኑና ተማሪዎቹ በፖሊሲ ሰነዶች ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸውን ከፍተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ምድብ ዓላማዎች ማለትም ትግበራ፣ ትንተና፣ ቅንበራና ግምገማ ችላ እንዲባሉ በሚያበረታታ መንገድ እየተዘጋጁ መሆናቸውን ማሳየቱ ፈተናዎቹ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ላይ ሊሳድሩት የሚችሉት ተጽዕኖ አሉታዊ ሊሆን እንደሚችል የሚያሳይ ነው፡፡ ምክንያቱም በሳዲክ (2010) ታይለር (2005)፣ ማደስ (1988)፣ ኦልድረሰንና ዎል (1993)፣ አበበ (1990) ስራዎች በግልጽ እንደተመለከተው ፈተናዎቹ ተማሪዎቹ እንዲማሯቸው፣ መምህራኑ እንዲያስተምሯቸው በሚጠበቁ ጉዳዮች ላይ አተኩረው የማይዘጋጁ ከሆነ፣ መምህራን ምንና እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው፣ እንዲሁም ተማሪዎች ምንና እንዴት መማር እንዳለባቸው እየመሩና አቅጣጫ እያሳዩ የሚመጡት ስርዓተ ትምህርቶቹ በመሆን ፈንታ ፈተናዎቹ መሆናቸው የማይቀር ነው፡፡ ይህም ፈተናዎች የመማር ማስተማር ሂደቱ በከፍተኛ ደረጃ የማሰብ ችሎታ ክሂሎች(Higher order thinking skills) ላይ እንዳያተኩር የሚያደርግ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዲያሳድሩ የሚያደርግ ነው፡፡ ከዚህም የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ /ብሔራዊ ፈተናዎች ሲዘጋጁ ለከፍተኛ የአዕምሯዊ ምድብ የትምህርት ዓላማዎች ተገቢ ትኩረት እንደማይሰጡና የክፍል ትምህርቱ/ የማስተማር-መማር ሂደቱ ዝቅተኛ የአዕምሮ ምድብ ችሎታ በሆኑት እውቀትና ግንዛቤ ላይ ትኩረት እንደሚያደርጉ መረዳት ይቻላል፡ ፡ ይህም ድርሳናቱ ሲከለሱ እንደተገለጸው ተማሪዎች ጥሩ ተናጋሪ፣ ጥሩ ጸሐፊ፣ ጥሩ አንባቢና ጥሩ አድማጭ እንዳይሆኑ የሚያደርግ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳደር የሚችል ነው፡፡

## ማጠቃለያና አስተያየት

በአጠቃላይ በአማርኛ ማጠናቀቂያ ፈተናዎችና በብሉም አዕምሯዊ ምድብ ችሎታዎች፣ መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ በአይነታዊና በመጠናዊ ዘዴዎች የተካሄዱት የውጤት ትንተናዎች በጣምራ እንዳሳዩት፤ አንደኛ በማጠናቀቂያ ፈተናዎቹና በአዕምሯዊ ምድብ ስድስት ችሎታዎች መካከል ያለው ተዛምዶ በሚጠበቀው ደረጃ አዎንታዊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ አሉታዊ ጎን የሚታይበት ብቻ ሳይሆን አሉታዊነቱ ጉልህና ጠንካራ ሆኖ ነው የተገኘው፡፡ በየትኛውም መለኪያ ሲታይ የ፪ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለሚያጠናቅቁ ተማሪዎች

የሚመጥን ፈተና ሆኖ አልተገኘም። ከአምሳና ስልሳ ዓመታት በፊት ሲተቹ እንደነበሩት ፈተናዎች ከ90% በላይ የሚሆኑት ጥያቄዎች የተማሪዎችን ዕውቀትና ግንዛቤ ብቻ የሚለኩ ናቸው። በዚህ ደረጃ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊመዘኑ ይገባቸው የነበሩት የመተግበር፣ የመተንተን፣ የማቀናበርና የመገምገም ችሎታዎች ከ10% በሚያንሱ ጥያቄዎች ብቻ እንዲወከሉ እየተደረገ ነው። ይህም የኢትዮጵያ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና አንደኛ Bloom እና ሌሎች (1956) እንዲህ ያለውን በዝቅተኛ ደረጃ አዕምሯዊ ችሎታ ላይ የሚያተኩር የፈተና ዝግጅት ችግር ለማስወገድ ያዳበሩትን የአዕምሯዊ ምድብ ክፍሎች እንደሚጻረር፤ ሁለተኛ፣ ቀደም ብለው የተገለፁትን በሀገሪቱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና በሥርዓተ ትምህርቱ ማስተግበሪያ ማዕቀፍ የተሰጡ የትኩረት አቅጣጫዎችን፣ በሚቃረን መልኩ እየተዘጋጀ እንደሆነ፣ ሦስተኛ ፈተናዎቹ በመማር -ማስተማር ሂደቶች ላይ ሊያሳድሩት የሚችሉት ተጽዕኖ አሉታዊ ሊሆን እንደሚችል ያሳያል።

የዚህም አንድምታ የፈተናዎች ኤጀንሲ አንደኛ፣ የሚመርጣቸው ጥያቄ አዘጋጆች/ ጸሐፊዎች እነዚህን ዓላማዎች ያገናዘቡ ጥያቄዎች የማውጣት/ የመጻፍ አቅም/ክሂል ያላቸው ላይሆኑ እንደሚችሉ ፤ ሁለተኛ፣ በኤጀንሲው ለየትምህርት ዓይነቶቹ ፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች እየተሰጠ ያለው የፈተና አዘገጃጀት አቅም ማጎልበቻ ስልጠና በባለሙያዎቹ ላይ የሚፈለገውን ለውጥ አስገኝቶ ፈተና አዘጋጆቹ (ጥያቄ ጸሐፊዎች) የሚያወጧቸው ጥያቄዎች፣ እነዚህን ዓላማዎች በፖሊሲውና በቋንቋው ትምህርት በተሰጣቸው ትኩረት መሰረት የሚወከሉበትን አቅጣጫ ማሳየት እያስቻላቸው እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው። ይህም የፈተናዎች ኤጀንሲ በእነዚህ ሁለት ጉዳዮች ላይ በተለይ የአማርኛ ፈተና ዝግጅትን በሚመለከት ሊያስብበት እንደሚገባ የሚያመላክት ጭምር ነው። ከእነዚህ ግኝቶች ላይ በመመስረትም የሚከተሉት አስተያየቶች ተሰጥተዋል፤ አንደኛ፣ አቅም ያላቸው ፈተና አዘጋጆችና የፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች የሚመረጡባቸው መስፈርቶች ቢዘጋጁ፤

ሁለተኛ ለፈተና አዘጋጆች(ጥያቄ ፀሐፊዎች)እና ለፈተና ዝግጅት ባለሙያዎች የሚያዘጋጇቸው ፈተናዎች ከትምህርቱ ጋር የሚጣጣሙ እንዲሆኑ ማድረግ የሚያስችሉ ጠንከር ያሉ ትምህርቶችና ስልጠናዎች የሚሰጥበት መንገድ ቢመቻች፤ ሦስተኛ፣ ለችግሮቹ መከሰት አንዱ መንስኤ ፈተናው በምርጫ ብቻ የሚቀርብ በመሆኑና በምርጫ ፈተና ከፍተኛ ደረጃ የአዕምሯዊ ችሎታዎችን መጠየቅ የተለየ ልምድንና ችሎታን ሊጠይቅ ስለሚችል በብዙ ሀገሮች እንደሚደረገው ፈተናው ምርጫ ብቻ እንዳይሆን የሚደረግበት መንገድ ቢፈለግ ።

## References


Abeba Hussen. (2008). *The effect of the Amharic language test on the teaching and learning of the 10th grade general secondary education.* Bahir Dar University; Master's Degree Thesis, (Unpublished.).

*General Education and Training Policy of the Transitional Government of Ethiopia.* 1994. Addis Ababa

Abebe, Bekele. 1990. *Principles of Curriculum.* Addis Ababa University. (Unpublished Teachng Material)

Abduljabbar , D.A.& N. Omar. 2015. Exam Questions Classification Based on Bloom`s Taxonomy Cognitive Level Using Classifiers Combination .*Jounal of Theortical & Applied Information Technology-* 78 (3).447-455.

Aldeson, J. C. 1999. Testing is too important to be Left to Testers. Lancaster Univirsity.

Alderson, J. C. Clapham, C. & Wall, D. 1995. Language Test Construction and Evaluation. Great Britain: CUP.

Anderson. L.W. Krathwohl. D.R. (Eds.) 2001. A Taxonomy for Learning, Teaching & Assessing; A revisen of Bloom`s Taxonomy of Educational Objectives; Coplete Edition.New yeork: Longman.

Chic, N. 2008. Using to in-class for in the context of V. *Journal of Science, Foreign Languages* 24 175183

Grouland, N.E 1986. *Measurement and Evaluation in Teaching.* New York: Macmillan.

Hughes, A. 2003. *Testing for Language Teachers.* Second editon.Cambridge: CUP

Cheng, L. 1997. How Does Washback Influence Teaching? Implications for Hong Kong. *Language and Education.* 11, 1: 38 – 54.

Douglas, D. 2010. Understanding Language Testing. HodderEducation; UK

Desalegn Chalchisa.2005. Comparative Study of Students` Achievement in English and Mathematics in Addis Ababa, Amhara and Oromo Reginal States of Ethiopia:

Ehel, R.L. 1979. *Essentials of Educational Mesurement.* (3rd edition.) New Jersey: Prentice Hall.

*Green*, A. 2007. IELTS Washback in Context Preparation for Academic Writing in Higher Education. Cambrige: CUP.

Grouland, N.E 1986. *Measurement and Evaluation in Teaching.* New York: Macmillan.

Hemming, G. 1987. A Guide to Language Testing . Heinle & Heinle Publishers: Boston.

Hughes, A. 2003.*Testing for Language Teachers.* Second editon.Cambridge: CUP.

Madaus, G. F. (1988). The influence of testing on the curriculum. In L. Travers (Ed.), *Critical issues in curriculum (87th yearbook of the Society for the Study of Education), Part 1* (pp.83-121). Chicago, IL: Chicago University Press

Minstry of Education. *2010. Curriculum Framework for Ethiopian Education* (KG-Grade 12).

Mulu, Nega and Daniel Tefera. 2005. *Introduction to Measurement and Evalution*. Addis Ababa University : Addis Ababa. (Unpublished Materil).

Munzenmaier ,Ms, and Rubin, N. *Perspectives: Bloom`s Taxonomy* :*What`s Old is New Again.*

Nuru Mohamed. (1992). *Levels of Questions: A Description of Textbook Exam Questions in Higher Secondary*

Rani,T.S. Priyadrsaini, J. R. and Bhaskara, D.R. 2004. Educational Measurment and Evalution. Darya Ganij; Arronk Offeset Press.

Sax. G. 1974. Principles of Educational Measurment and Evalution.Califonia: Washington Publishing Company.

Shohamy, E., Donitsa-Schmidt, S., & Ferman, I. (1996). 'Test impact revisited: Washback effect over time'. *Language Testing. 13/3,* 298-317.

Siddiek, A.G. (2010). The Impact of Test Content Validity on Language Teaching and Learing Asian Social Science.vol6, No. 12 December.

Tangsakul,P. Kijpoonphol, W. Duy Linh,N. & Kimura, L. N. 2017. Using bloom's revised taxonomy to analyze reading comprehension questions in team up in English 1-3 and grade 9 English o-net tests. *InternationalJournal of Research - Granthaalayah*, Vol.5 (Iss.7):

Taylor, L. 2005. *Washback and impact. ELT Journal,* 59(2), 154-155.

Veeravagu, J. Muthusamy.C. Marimuthu, R. & Subrayan, A. 2010. Using Bloom's Taxonomy to Gauge Students' Reading Comprehension Performance. Canadian Social Science. 6, (3). pp. 205-212

Wall, D. 2005. *The impact of high-stakes examinations on classroom teaching: A case study using insights from testing and innovation theory.* Cambridge: Cambridge University Press**.**

Weir, C. J, A. Hughes and D. Porter. 1990. Reading Skills: Hierarchies, Imlicational Relationships and Identiiablity. In Reading in a Foreigh Language, vol 7 Nub1 Autumn 1990 PP.505-510. *Jounal of International Education Centre.*College of St.Mark& St. John. Pymouth,England.